# 4ቱ
# የሐዋርያው ጳውሎስ ደብዳቤዎች ፡
# ወደ ቆላስይስ ሰዎች፣
# 1ኛጢሞቴዎስ፣2ኛጢሞቴዎስ
# እና ወደ ቲቶ




<u>በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልግሎት የተዘጋጀ ሴፕቴምበር 2022</u>

ማውጫ አርዕስት ገፅ ....1

**ክፍል አንድ:የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክትወደ_ቆላስይስ ሰዎች** ....2

**የመልዕክቱ ይዘት እና አወቃቀር_** ....3

**ጥናት 1: የጳውሎስ ሰላምታና የምስጋና ጸሎት** ....7

**ጥናት 2: የጳውሎስ የልመና ጸሎት** ....8

**ጥናት**3: **የክርስቶስ መለኮትነትና ፍጹም ሰውነት** ....9

**ጥናት** 4:**የሐ .ጳውሎስ መስዋዕታዊ አገልግሎት** ....10

**ጥናት 5: ክርስቶስን ማወቅ /Knowing Christ/** ....11

**ጥናት**6: **ፍልስፍና ሳይሆን ,ክርስቶስ/ Not Philosophy ! But Christ ! /** ....12

**ጥናት** 7: **ሕግ ሳይሆን ክርስቶስ** /Not Legalism,But Christ/ ....13

**ጥናት** 8: **በመላዕክት ሳይሆን በክርስቶስ** /Not Mysticism ,But Christ/ ....14

**ጥናት**9:**በላይ ያለውን እሹ** /Practice of Christ -Mind Set Up/ ....15

**ጥናት** 10: **አሮጌውን አውልቁ** /Putting off Old Nature/ ....16

**ጥናት** 11: **አዲሱን ልበሱ /Putting on The New Nature/** ....17

**ጥናት**12: **የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት** ....18

**ጥናት 13: ክርስቲያናዊ ቤተሰብ** / The Christian Home/ ....19

**ጥናት 14:** ክርስቲያን በስራ ቦታ/Christian at Workplace/ ....20

**ጥናት15:**ክርስቲያን በዓለም/ Christian in the World/ ....21

**ጥናት** 16: **ማጠቃለያና የስንብት ቡራኬ**/ Closing Exhortations & Blessings/ ....22

# ክፍል ሁለት:የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ለጢሞቴዎስ <u>አንደኛ</u> ....23

**መግቢያ** ....24

**ጥናት 1: ከሐሰተኛ መምህራን መጠበቅ** ....26

**ጥናት 2: <u>ለጳውሎስ የተሰጠዉ ጸጋ</u>** ....27

**ጥናት**3: **የአምልኮ መመሪያክፍል1** ....28

**ጥናት**4: **የአምልኮ መመሪያክፍል2** ....29

**ጥናት** 5: የእረኞች መመዘኛ ....30

**ጥናት** 6: **<u>የዲያቆናት መመዘኛ</u>** ....31

**ጥናት** 7: **ለጢሞቴዎስ የተሰጠ መመሪያ** ክፍል 1 ....32

**ጥናት 8:** ለጢሞቴዎስ የተሰጠ መመሪያ ክፍል 2 ....33

**ጥናት9**: ስለ መበለቶች፤ ሽማግሌዎችና ባሪያዎች የተሰጠ መመሪያ ክፍል 1 ....34

**ጥናት 10:** ስለ መበለቶች፤ ሽማግሌዎችና ባሪያዎች የተሰጠ መመሪያ ክፍል **2** ....35

**ጥናት 11: <u>የገንዘብ ፍቅር</u>** ....36

**ጥናት 12: ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው አደራ** ....37

ክፍል ሦስት የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ለጢሞቴዎስ ሁለተኛ ........ 38
**መግቢያ ........ 39**
**ጥናት 1: ስለታማኝነት ማበረታቻ ክፍል1 ........ 41**
**ጥናት 2: ስለታማኝነት ማበረታቻ ክፍል2 ........ 42**
**ጥናት 3: ስለ ትዕግስት የቀረበ ጥሪ ........ 43**
**ጥናት 4 እግዚአብሔር የሚቀበለው አገልጋይ ........ 44**
**ጥናት 5: የመጨረሻው ዘመን ክህደት ........ 45**
**ጥናት 6: የጳውሎስ አደራ ለጢሞቴዎስ........ 46**
**ጥናት 7: የሐዋርያው ጳውሎስ ሩጫ ፍጻሜ ........ 47**
ክፍል አራት: የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ለቲቶ ........ 48
**መግቢያ ........ 49**
**ጥናት 1: ሰላምታና ሽማግሌዎችን ለመሾም ለቲቶ የተሰጠው መመሪያ ........ 51**
**ጥናት 2: ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ለቲቶየተሰጠ መመሪያ** ........ 52
**ጥናት**3: **አማኞች የተሰጠ መመሪያ ........ 53**
**ጥናት** 4ቅዱስ ጥሪ እና የአማኞች ሃላፊነት ........ 54
**ጥናት 5: ክርስቶስን መምሰል** ........ 55
**ጥናት**6: **የመጨረሻ ሰላምታ እና ምክር ........ 56**

# <u>ክፍል አንድ</u>

## የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት
## <u>ወደ ቆላስይስ ሰዎች</u>



**<u>የመልዕክቱ ይዘት እና አወቃቀር</u>**

## I. መግቢያ

1.1 ታሪካዊ ዳራ/Background/

1.2 ዓላማና ጭብጥ/Purpose & Theme /

1.3 ልዩ -ገጽታ/Unique of the Epistle1/

## II. ዋና መልዕክት/ Main Message /

2.1 የመግቢያ ሰላምታ/Introductory Greetings/

2..2 የክርስቶስ መለኮትነትና ፍጹም ሰውነት/The Deity and Humanity of Christ/

2 .3. በቈላስይስ የነበረው የሐሰት ትምህርት መሰረቶች

2. 3.1 የሰዎች ፍልስፍና /Human Philosophy/

2.3.2. የአይሁድ ሕግ/ Jewish Law/

2.3.3. የአሕዛብ ልማዳዊ አምልኮት/Pagan's Religions Beliefs/

## III. አፅንዖተ ምክርና የመዝጊያ ሰላምታ /Concluding Remarks and Final Greetings/

3.1 አማኙ ሊኖረው ስለሚገባው ክርስቲያናዊ ስነ - ምግባር /Life Applications/

3.2 ማጠቃለያና የስንብት ቡራኬ/ Closing Exhortations & Blessings/

## 1. **መግቢያ**

### 1.1 **ታሪካዊ ዳራ /Background/**

የቈላስይስ ከተማ ከኤፌሶን በስተ ምስራቅ 160 ኪ.ሜ ርቀት በትንሹ እስያ ደቡብ ምዕራብ በፍርግያ ግዛትከሎዶቅያ አጠገብ ትገኝ ነበር። / Diversified Community/- A small Town under Roman Empire, least important city politically and economically/.

**ጸሓፊው**

በቈላ " *4: 18* " በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ ነው። " ስለሚል ጸሓፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን የተጻፈበት ዘመን በ6.2 ዓ.ም ሳይሆን አይቀርም ።

**የቈላስይስ ቤክ እንዴት ተመሰረተች** ?

የቆላስይስ ቤ/ክ መመስረት ጳውሎስ በኤፌሶን ከተማ ለሦስት ዓመት የነበረው ስኬታማ አገልግሎት ውጤት ነው ። ሐዋ 20:31 / ጳውሎስ ከቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን በአካል ሁሉንም ባያውቅም ስለ እነርሱ መንፈሳዊ ሕይወት እጅግ ይገደው ነበር ። ከመንፈሳዊ ልጆቹ አንዱ በሆነውና በአገልግሎትም በመጠመድ አብሮት ያገለግል በነበረው የቈላስይስ ከተማው ሰው ምናልባት የቁላስይስ ቤ/ክርስቲያ መሪና መሥራች የሆነው ኤጳፍራ አማክይነት ከቤ/ክቱ ጋር ግንኙነት ነበረው ። /1:7;4:12/ ጳውሎስ በዚህ ጊዜ እስረኛ ነበረ ። በዚያን ጊዜም ስለ እርሱ ደግሞ የታሰርሁበትን የክርስቶስን ምሥጢርእንድንነግር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ ።/ ምናልባትም በሮም እስር ቤት ሆኖ ወደ ቄሳር ይግባኝ በማለት ውጤቱን ይጠባበቅ ነበር; ። ጳውሎስን በመወከል ይህን መልዕክት ለቈላስይስ ቤክርስቲያን ወስዶ ያስረከበው ከጳውሎስ ጋር አብሮ ያገለግልየነበረው ቲኪቆስ ነው ። የተወደደ ወንድምና የታመነ አገልጋይ በጌታም አብሮኝ ባሪያ የሆነ ቲኪቆስ ኑሮዬን ሁሉ ያስታውቃችኋል ። /4:7/

### 1.2. **ዓላማና ጭብጥ/Purpose & Theme /**

ሐ.ጳውሎስን ይህን መልዕክት ለመጻፍ ያነሳሳሳው የቁላይስን ቤክርስቲያን የወደ ፊት መንፈሳዊ ሁኔታ አደጋ ላይ የሚጥሉየሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ብቅ ማለት ነበር ። ሐሰተኛ ትምህርቶቹም የተመሰረቱት :

1. የሰዎች ፍልስፍና /Human Philosophy/
2. የአይሁድ ሕግ /Jewish Law/
3. የአሕዛብ ልማዳዊ አምልኮት/ Pagan's ReligionsBeliefs/ ነበር ።

ስለዚህ የቈላስይስ መልዕክት ዋና ዓላማ :

- የክርስቶስን መለኮትነት እና ፍጹም ሰውነት ለማስረዳት
- በቈላስይስ የነበረውን አደገኛ የሐሰት ትምህርት ለመዋጋት እና
- በክርስቶስ የሚገኘው አዲስ ሕይወት ምን እንደሚመስልና ከአማኙ ስለሚጠበቀው ክርስቲያናዊ ስነምግባር በአጽንዖት ለመምከር ነው።

1.3 ልዩ -ገጽታ/Unique of the Epistle1/

**የቈላስይስን መልዕክት ሦስት ዋና ዋና ገጽታዎች ልዩ ያደርጉታል ፡**

1. ከሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይልቅ የቈላስይስ መልዕክት በክርስቶስ የበላይነትና አማኝ በእርሱ ውስጥ ባለውፍጹምነት ጣምራ እውነት ላይ ያተኩራል

2. ክርስቶስ ፍጹም መለኮት እንደሆነ አጠንክሮ የሚገልጽ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ክብሩን በተመለከተ ከሚጠቀሱትዋና ዋና ክፍሎች አንዱ የሚገኘው በዚህ መልዕክት ውስጥ ነው። /2:9; 1:15-23/

3. የቈላስይስ መልዕክት ይዘቱ ከኤፌሶን መልዕክት ጋር ስለሚመሳሰልና ሁለቱም የተጻፉበት ጊዜ ተመሳሳይ ስለሆነአንዳንድ ጊዜ ተወራራሽ ሁለት መልዕክቶች በመባል ይታወቃሉ ።

## ጥናት 1

## የጳውሎስ ሰላምታና የምስጋና ጸሎት

## የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 1:1-8

**መግቢያ:** በዛሬው የመጀመሪያ ጥናታችን ሐ .ጳውሎስ ለቆላስይስ አማኞች ያቀረበውን ክርስቲያናዊ ሰላምታ፣ ስላላቸው እምነት ፥ ፍቅርና በሰማይ የተዘጀላቸውን ተስፋ ያቀረበውን ምስጋና እንዲሁም የተወደደው ኤጳፍራ እንደ ክርስቶስ አገልጋይ የነበረውን መልካም ባሕርይ እንመለከታለን ።

**ዐውደ ምንባባችን:**

1. ከቁ 1-2 ሐ ጳውሎስ ስለ ሐዋርያነት ስልጣኑ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ብሎ የማስተዋወ ፋይዳ ምን ይመስላችኋል ? በሰላምታው በቄላስይስ ለሚኖሩ ቅዱሳን ያቀረበላቸውን የማበረታቻ ቃላቶች / **Words of Encouragement**/ ዘርዝሩ።

2. ከቁ 3-6 :ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት ምክንያት የቄልስይስ አማኞች :

. በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋ የተነሳ
. በክርስቶስ ስላላቸው እምነት
. ለቅዱሳን ሳላላቸው ፍቅር
. በዓለምም ፍሬ ስለሚያፈሩና ስለሚያድጉ ነው።

**ጥያቄ 1:** ከእነዚህ የማመስግኛ ነጥቦቹ ያገኛችሁትን መረዳት ለቡድናችሁ አጋሩ።

3. ከቁ 7-8 ሐ. ጳውሎስ ስለ ቄላስይስ ቤ/ክ መንፈሳዊ ሁኔታ ከማን ሊሰማ/ ሊያውቅ የቻለው ከተወደደ የክርስቶስ አገልጋይ ከኤጳፍራ ነው ።

**ጥያቄ2:** ይህ አገልጋይ የተወደደበት ባሕሪው ምን ዓይነት ነው ? ስለ ቆላስይስ አማኞች ለዻውሎስ ያስታወቀውስ ምናቸውን ነበር ?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

4. ከሐ.ጳውሎስ የማበረታቻ እና የምስጋና መልእክስት ከተወደደው አገልጋይ ከኤጳፍራ ባሕርይ እና አጠቃላይ የቆላስይስ አማኞች ከተወደሱበት መንቸሳዊ ሕይወትበዚህ ዘመን ያለን እኛ ምን እንማራለን ?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

በዚህም ዘመን የምንገኝ አማኞች እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ አማኞች በውስጣቸው ስላለው መልካም ነገር ማበረታታና ማመስገን፣ የከበረውንና ከፍ ያለውን ተስፋ ደግሞ ማሳየት እንዲሁም እንደ ተወደደው ወንድም ኤጳፍራ የክርስቶስ አገልጋይ ባሕርይን መያዝ ይጠበቅብናል ።

**የቃል ጥቅስ**

“ ስለ እናንተ ስንጸልይ፥ በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋ የተነሣ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እምነታችሁ ለቅዱሳንም ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተን፥ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እናመሰግናለን፤ “ ቆላስይስ 1:5

## **ጥናት 2**

## የጳውሎስ የልመና ጸሎት

## **የምንባብ ክፍል:ቆላስይስ 1:9-14**

**መግቢያ:** ባለፈው ጥናት ሐ .ጳውሎስ ለቆላስይስ አማኞች ያቀረበውን ክርስቲያናዊ ሰላምታ፣ ስላላቸው እምነት ፥ ፍቅርና በሰማይ የተዘጀላቸውን ተስፋ ያቀረበውን ምስጋና እንዲሁም የተወደደው ኤጳፍራ እንደ ክርስቶስ አገልጋይ የነበረውን መልካም ባሕርይ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሐ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ከጸለያቸው አራት ታላላቅ ሐዋርያዊ ጸሎቶች መካከል አንዱ የሆነውን ለቆላስይስ አማኞች በ ጥ ል ቀ ት ሲጸልይልይላቸው በዝርዝር እንመለከታለን ።

**ዐውደ ምንባባችን:**

1. በቁ 9 ሐ.ጳውሎስ ለቈላስይስ አማኞች በሶስት ርዕሰ ጉዳዮች ጸለየ ። እነዚህም
   - ✓ የፈቃዱ እውቀት /The Knowledge of His Will /
   - ✓ መንፈሳዊ ጥበብ / Wisdom /
   - ✓ መረዳትን ሁሉ እንዲሞላባችሁ/ All Understanding/ ናቸው ።
1. ከቁ 10-12 ሐ. ጳውሎስ ቈላስይስ አማኞች ሰባት ተግባራዊ የክርስትና መገለጫዎን በሕይታቸው እውን በማድረግ ለጌታ እንደሚገባ ይመላለሱ ዘንድ ይጸልያል። እነዚህም:

   “ 1. በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እንዲያፈሩ 2. በእግዚአብሔር እውቀት እንዲያድጉ 3.ጌታን ደስ እንዲያሰኙና እንዲያከብሩ 4. ታላቅ ጽናትና ትዕግስት ይኖራቸው ዘንድ 5. በእግዚአብሔር ኃይል እንዲበረቱ/እንዲሞሉ 6. በጌታ ደስ እንዲሰኙና 7. እግዚአብሔር አብን እንዲያመሰግኑ እንለምናለን “ የሚሉ ናቸው ።

**ጥያቄ 2**: እነዚህ ተግባራዊ የክርስትና መገለጫዎን ምን ማለት እንደሆኑ የተረዳችሁትን ለቡድናችሁ አጋሩ ።

2. ከቁ 12-14 ሐ.ጳውሎስ ለቈላስይስ አማኞች በክርስቶስ ይህ ሆነልን እያለ አምስት ትላልቅ መንፈሳዊ በረከቶች :

   1.በቅዱሳንም ርስት እንድንካፈል ያበቃንን 2. ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ 3. ቤዛ ሆነልን 4. የኃጢአትን ስርየት አገኘን 5. ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን በማለት ያስታውሳቸዋል ።

**ጥያቄ 3**: እነዚህ መንፈሳዊ በረከቶች ምን ማለት እንደሆኑና እነዚህን መረዳት አስፈላጊነት ተወያዩ ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

**ጥያቄ 4**: የጥበብ ሁሉ መዝገብ ሁሉ በእርሱ የሆነውን **ክርስቶስን ለማወቅ** ከምናደርጋቸው መንፈሳዊ ነገሮች ጥቂቱን ለቡድናችሁ አጋሩ ።

**ጥያቄ 5**: በየእለቱ የሕይወት ጉዞአችን በተግባራዊ የክርስትና ለመገለጥ ምን ያህል እንተጋለን ?

- ❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

ሐ.ጳውሎስ የቆላስይስ አማኞች የእግዚአብሔርን የፈቃድ እውቀት የሆነውን ክርስቶስን በብዙ የመረዳት ብልጽግና እንዲያውቁት እንደ ጸለየላቸውና በዚህም ተግባራዊ ሕይወት እንዲገለጡ እንዳበረታታቸው ሁሉ እኛም ሕይወታችንን በዚህ ልክና ደረጃ ልንቃኘው ይገባል ።

- **ማስታወሻ**: ሌሎቹ ሦስቱ ሐዋርያዊ ጸሎቶች የሚገኙት በኤፌ1:16-19 እና በፊል 1:9-11 ነው ።

**የቃል ጥቅስ**

ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም። **ቆላስይስ 1:9**

**<u>ጥናት 3</u>**

**የክርስቶስ መለኮትነትና ፍጹም ሰውነት**

**<u>የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 1:15-23</u>**

**<u>መግቢያ:</u>** ባለፈው ጥናት ሐ.ጳውሎስ ለቆላስይስ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ከጻለያቸው አራት ታላላቅ ሐዋርያዊ ጸሎቶች መካከል አንዱ የሆነውን ለቆላስይስ አማኞች በ ጥ ል ቀ ት ሲጸልይልይላቸው በ ዝ ር ዝ ር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐ.ጳውሎስ ለቈላስይስ አማኞች የክርስቶስ መለኮትነትና ፍ ጹ ም ሰ ው ነ ት አ ስ ረ ግ ጦ ያ ስ ረ ዳ በ ት ን በ ዝ ር ዝ ር እ ን መ ለ ከ ታ ል ን።

**<u>ዐውደ ምንባባችን:</u>**

1. ከቁ 15-17 ሐ.ጳውሎስ ለቈላስይስ አማኞች የክርስቶስ መለኮትነት በሰባት መንገድ አስረግጦ ያስረዳል። እነዚህም እውነቶች: የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው።

 2. ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል/Over Creation //False Teachers believe Physical World by itself Was Evil/ 3. ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው ። 4 ከሙታንም በኵር ነው።

 5 . ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል። / Sustainer /-ሁሉም ነገር ተያይዞ የጸናው በእርሱ ነው ማለት ነው ።

 6. እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው ። 7. ክርስቶስ አምላክ ነው ። የሚሉት ናቸው ።

**<u>ጥያቄ</u> 1:** እነዚህ እውነቶች እያንዳንዳቸው ምን ማለት እንደሆኑ የተረዳችሁትን ለቡድናችሁ አጋሩ ።

**2.** ከቁ 19—22 “ እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው ። እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ **ከሙታንም በ<u>ኵር</u>** ነው። *19-20* እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ በእርሱም በኩል **<u>በመስቀሉ ደም</u>** ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና ። *21-22* እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፥ በፊት የተለያችሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን **<u>በሥጋው ሰውነት</u>** **<u>በሞቱ</u>** በኩል አስታረቃችሁ።”

**<u>ጥያቄ</u> 2.** ሐ.ጳውሎስ ለቈላስይስ አማኞች የክርስቶስን ፍ ጹ ም ሰ ው ነ ት ለ ማ ስ ረ ዳ ት የ ተ ጠ ቀ መ ባ ቸ ው ን ቃ ሎ ች ዘ ር ዝ ሩ ።

**<u>ጥያቄ 3</u>**: እነዚህ እውነቶች እያንዳንዳቸው ምን ማለት እንደሆኑ የተረዳችሁትን ለቡድናችሁ አጋሩ ።

**<u>ጥያቄ 4</u>**. በቁ *23* ይህም፥ ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ፥ በሃይማኖት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል ። ማለት ምን ማለት ነው ?

**<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>**

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**<u>ጥያቄ 5</u>**. የክርስቶስን ሉአላዊ አምላክነትና ፍጹም ሰውነት በግላችን የተረዳነውን ለቡድናችን እናጋራ ።

**<u>ማጠቃለያ</u>**

በአለም ላይ ብዙ አማልክት እና ኃይማናቶች በየዘመኑ ቢኖሩም ፍፁም ሰው ሆኖ ስለ እኛ በመስቀል ተሰቅሎ የሞተልን የማናፍርበት እውነተኛና ዘላለማዊ አምላክ ክርስቶስ ብቻ ነው።

**<u>የቃል ጥቅስ</u>**

“ እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው ። “ ቆላስይስ 1:16

“ እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና ። ” ቆላስይስ 1:20

# ጥናት 4

## የሐ .ጳውሎስ መስዋዕታዊ አገልግሎት

## የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 1:24-29

**መግቢያ:** ባለፈው ጥናት ሐ.ጳውሎስ ለቆላስይስ አማኞች የክርስቶስ መለኮትነትና ፍጹምሰውነት አስረግጦ ያስረዳበትን በጥልቀትበዝርዝር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የሐ.ጳውሎስ መስዋዕታዊ አገልግሎት ምን ይመስል እንደነበር በዝርዝር እንመለከታለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች:**

1. *በቁ 24* ሐ.ጳውሎስ " ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጐደለውን እፈጽማለሁ ።" ሲል ይህ ሐሳብ የክርስቶስ መስቀል ሞት ለድነታችን በቂ አይደለም ማለቱ ሳይሆን በክርስቶስ የመስቀል ስራ አምኖ የዳነው ጳውሎስ የክርስቶስን ወንገል ለሌሎች ሲያደርስ ስለሚደርስበት መከራ መግለጹ ነው ።

**ጥያቄ 1:** ሐ.ጳውሎስ አሁን **በመከራዬ** ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፥ ያለበት ሚስጥሩ ምን ይመስላችኋል ?

*25.*ስለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት፥የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ ።*26* ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው፥

**ጥያቄ 2:** ሐ.ጳውሎስ ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል የሚለው ምሥጢር ምንድር ነው ?

**ጥያቄ 3:** *በቁ 27* "ለእነርሱም እግዚአብሔር **በአሕዛብ** ዘንድ ያለው **የዚህ ምሥጢር ክብር** ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ **ሊያስታውቅ** ወደደ፥ **ምሥጢሩም** የክብር ተስፋ ያለው **ክርስቶስ** በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው ። "ከሚለው ቃል የተረዳችሁትን አካፍሉ ።

**ጥያቄ 4:** *በቁ 28"* እኛም በክርስቶስ **ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ** ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው **እርሱ** ነው ። "ከሚለው ቃል የሐ.ጳውሎስ የአገልግሎቱ ዓላማ ምንድርን ነው ? የመልዕክቱ ማዕከልስ ማነው

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

**ጥያቄ 5:** *በቁ29 "* ለዚህም ነገር ደግሞ፥ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ፥ እደክማለሁ።" "ከሚለው ቃል ሐ.ጳውሎስ ክርስቶስን ማዕከል ባደረገው አገልግሎቱ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ሙላት ላት ለማድረስ መጋደሉን ስናይ ከእርሱ መስዋዕታዊ የአገልግሎት ሕይወቱ በዚህ ዘመን አገልጋዮች ለሆነው ለእኛ የቀረልንን መረዳት ካለ ለቡድናችሁ በአጭሩ አጋሩ ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

ሐ.ጳውሎስ ክርስቶስን ማዕከል ባደረገው አገልግሎቱ ለአህዛብ ሁሉ ክርስቶስን ለማስተዋወቅና አማኞችን ወደ ክርስቶስ ሙላት ለማድረስ በክርስቶስ መከራ ይካፈል ዘንድ ስለ ተፈቀደለት ሐሴት እያደረገ የወንጌል ተጋድሎ ያደርጋል ።ውን ይፈጽማል ። ከእኛም የሚጠበቀው ከዚህ ያነሰ አይደለምና ዛሬ ነገ ሳንል እንወስንና የምንችለውን ማድረግ እንጀምር ። ጌታም የሚያስችለንን ጸጋ ይሰጠናል ።

**የቃል ጥቅስ**

" አሁን በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፥ ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጐደለውን እፈጽማለሁ። ቆላስይስ 1:24

## ጥናት 5

## ክርስቶስን ማወቅ /Knowing Christ/

## የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 2:1-5

**መግቢያ** : ባለፈው ጥናት ሐ.ጳውሎስ ለቆላስይስ አማኞች ያሳየውን መስዋዕታዊ አገልግሎት ምን ይመስል እንደነበር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የእግዚአብሔር ሚስጥር የሆነውን ክርስቶስን እንዲያውቁ በድጋሚ ያደረገውን የጸሎት ተጋድሎ እናያለን ።

**ዓውደ ምንባባችን:**

ቁ *1* ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት ፊቴንም በሥጋ ስላላዩት ሁሉ እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና።
ቁ *2.* ልባቸው እንዲጸናና፥ በፍቅርም ተባብረው በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት ባለ ጠግነት ሁሉ እንዲደርሱ **የእግዚአብሔርንም ምሥጢር** እርሱንም ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ ። *3* የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና ።

**የሐ .ጳውሎስ ተጋድሎ የቆላስይስ አማኞች**

1. **በማስተዋል**/ Wisdom/ **እንዲያድጉ**
2. **የመረዳትን** ብልጽግና /All Understanding/ **እንዲያገኙ**
3. የእግዚአብሔር **ሚስጥ**ር የሆነውን ክርስቶስን **እንዲያውቁ** /Knowing Christ/
4. ልባቸው እንዲጸናና
5. እርስ በርስ በፍቅር እንዲተሳሰሩ ነበር ።

**ጥያቄ 1**: የእነዚህ ሐሳቦች ትርጉም ምን ማለት እንደሆኑ እያንዳንዳቸውን አብራሩ ።

**ጥያቄ 2**: ሐ .ጳውሎስ በእነዚህ መሰረታዊ ሐሳቦች ላይ ተመርኩዞ ለቆላስይስ አማኞች በመጋደሉ በዋነኛነት ሊያሳካ የፈለገው ዋነኛ ዓላማ ምን ይመስላችኋል?

ቁ.4 "ማንም በሚያባብል ቃል እንዳያስታችሁ ይህን እላለሁ።

ቁ5. በሥጋ ምንም እንኳ ብርቅ፥ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝና፥ ሥርዓታችሁንም በክርስቶስም ያለውን የእምነታችሁን ጽናት እያየሁ ደስ ይለኛል ።

**ጥያቄ 3**: ብዙ የሚያባብሉ አሳች ቃላቶች በበረከቱበት ዘመን በክርስቶስ ያለውን እምነት አፅንቶ መቆየት እንዴት የሚቻል ይመስላችኋል ?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

**ጥያቄ 4**: የእግዚአብሔር ሚስጥር የሆነውን ክርስቶስን በሕይወታችን ይበልጥ ለማወቅ በየዕለቱ ከምናደርጋቸው ነገሮች ጥቂቶቹን ለቡድናችሁ አጋሩ ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

ከሚያባብሉ የሰዎች ቃላት ተጠብቅን ታውቆ የማይጨረሰውን የእግዚአብሔር ሚስጥር የሆነውን ክርስቶስን እለት እለት በማወቅ በእርሱ ያለንን እምነት አፅንተን ልንይዝ ይገባናል ።

**የቃል ጥቅስ**

"የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና።" ቆላስይስ 2:3

## **ጥናት 6**

### **ፍልስፍና ሳይሆን , ክርስቶስ/ Not Philosophy ! But Christ ! /**

### **የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ2፥6-10**

**መግቢያ**: ባለፈው ጥናት ሐ.ጳውሎስ ለቆላስይስ አማኞች የእግዚአብሔር ሚስጥር የሆነውን ክርስቶስን እንዲያውቁ በድጋሚ ያደረገውን የጸሎት ተጋድሎ ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የቈላስይስ አማኞች ከሰዎች ወይም ከዓለማዊ ፍልስፍና ጋር ተያይዞ ከተንሰራፋው የሐሰት ትምህርት እንዲጠበቁ የሰጣቸውን ምክር በዝርዝር እናያለን ።

**ዓውደ ምንባባችን:**

ከቁ 6-8 ባለው ክፍል ሐ.ጳውሎስ ለቆላስይስ አማኞ ክርስቶስ ያውቁ ዘንድ *ወደ 6 የሚጠጉ* ትላልቅ ምክሮችን ይለግሳቸዋል ። እነዚህም :

1. በእርሱ ተመላለሱ
2. በእርሱ ስር ስደዱ */Like a tree/*
3. በእርሱ ታነጹ/ Like a building/
4. በኃማኖት ጽኑ
5. በብዙ አመስግኑ
6. ከከንቱ ፍልስፍና ተጠበቁ የሚሉ ናቸው ።

**ጥያቄ 1:** እነዚህ ምክረ-ሐሳቦች እያንዳንዳቸው ምን ማለት እንደሆኑ የረዳች ሁትን ለቡድና ችሁ አጋሩ።

**ጥያቄ 2:** *በቁ9 ላይ* ሐ.ጳውሎስ "በእርሱ **የመለኮት ሙላት** ሁሉ **በሰውነት** ተገልጦ ይኖራልና ። " ሲል ምን ማለቱ ነው ?

**ጥያቄ 3** *በቁ10 ላይ* ሐ.ጳውሎስ " ለአለቅነትና ለሥልጣንም ሁሉ **ራስ በሆነ** በእርሱ ሆናችሁ **ተሞልታችኋል**። " ሲል ምን ማለቱ ነው ?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

**ጥያቄ 4:** በዚህ ዘመን ከክርስቶስ ትምህርት ዘወር ሊያደርጉን ከሚሞክሩ በርካታ የዓለም ከንቱ ፍልስፍናዎች ከምታውቋቸው ውስጥ ጥቂቶቹን ጥቀሱ። ፍልስፍናዎቹ የሚያተኩሩትስ ምን ላይ ነው ?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

በዚህ ዘመን በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ የተመሰረተውን ክርስትና ከሚፈታተኑ ታላላቅ ፍልስፍናዎች አንዱ በሰው ምድራዊ ማንነት ላይ የሚያተኩረው አስተሳሰብ ነው። ይህ አመለካከት በአጠቃላይ በዓለማዊ ትምህርት፣ አስተዳደርና ኅብተረተሰብ ውስጥ ዋና ፍልስፍናና ተቀባይነትን አግኝቶ እንደ ሃይማኖት እስከመቆጠር ደርሷል ። በዓለም በሚገኙ ሚዲያዎች፣ የዝናኛ ፕሮግራሞችና ማኅበራዊ ትስስር ገፆች ትኩረት የሳበ ጉዳይ መሆን እየቻለ ነው ። ሐዋርያው ጳውሎስ ከክርስቶስና ከተፃፈው ቃሉ ወጥቶ የሰውን ስርዓት የሚያጎላ ፍልስፍናን አጥብቀን እንድንቃወም ያስጠነቅቀናል ። ከእንዲህ ዓይነቱ የዘመኑ የፍልስፍና ማዕበል ራሳችንን እና ቤተክርስቲያንን በክርስቶስ ትምህርት መጠበቅ እንድንችል ጸጋው ያግዘን ።

**የቃል ጥቅስ**

" እንደ **ክርስቶስ ትምህርት** ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ **በፍልስፍና በከንቱም መታለል** ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ ። " ቆላስይስ 2:8

## ጥናት 7

### ሕግ ሳይሆን ክርስቶስ /Not Legalism,But Christ/

### የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 2: 11-17

**መግቢያ:**ባለፈው ጥናት ሐ.ጳውሎስ የቈላስይስ አማኞች ከሰዎች ወይም ከዓለማዊ ፍልስፍና ጋር ተያይዞ ከተንሰራፋው የሐሰት ትምህርት እንዲጠበቁ የሰጣቸውን ምክር በዝርዝር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ከነሕግጋቱ ክርስቶስ እንደደመሰሰውና እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ በማስወገድ ነፃ እንዳወጣን ሐ.ጳውሎስ ያስረዳበትን በዝርዝር እናያለን ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ***በቁ. 11 ላይ*** ሐ.ጳውሎስ ″ **የሥጋንም ሰውነት በመገፈፍ፥** በክርስቶስ መገረዝ፥ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ።ሲል ምን ማለቱ ነው ?
2. ***በቁ. 12 ላይ*** ሐ.ጳውሎስ ″በ**ጥምቀትም** ከእርሱ ጋር **ተቀብራችሁ**፥ **በጥምቀት** ደግሞ፥ ከሙታን **ባስነሣው** በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ፥ከእርሱ ጋር **ተነሣችሁ** "ይላል። ትንሳዔ ለኛ ምንድር ነው ?
3. ***በቁ 13 ላይ*** ሐ.ጳውሎስ እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ። በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ"ይላል። የክርስቶስ ይቅርታ ያስገኘልን ምን ዓይነት ሕይወት ነው ?
4. ***በቁ 14 ላይ*** ሐ.ጳውሎስ " በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን **የዕዳ ጽሕፈት** ደመሰሰው ። እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል "ይላል።በክርስቶስ የተደመሰሰልን ይህ **የዕዳ ጽሕፈት** ምን የሚል ሕግ ነበር ?
5. ***በቁ 15 ላይ***"አለቅነትንና ሥልጣናትን **ገፎ**፥ ድል በመንሣት በእርሱ **እያዞራቸው** በግልጥ አሳያቸው። " ሲል ምን ማለቱ ነው ?
6. ***በቁ 16 ላይ***"አለቅነትንና እንግዲህ **በመብል ወይም በመጠጥ** ወይም **ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ** ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ ። "ሲል ምን ማለቱ ነው ?

## ከሕይወት ጋር ማዛመድ

7. ከተጻፈብን የሕግ እርግማን በክርስቶስ ነፃ መውጣታችንን በየዕለቱ እያስታወስነው ምን ያህል ደስ እንሰኝበታለን ?
8. ***በቁ 17 ሐጳውሎስ*** ″ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፥ አካሉ ግን **የክርስቶስ** ነው ።" እያለ አንዳንድ የኃይማኖት ድርጅቶች በአዲስ ኪዳንም ዘመን በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕጎች ለሞኖሩት ምን ማድረግ የሚጠበቅብን ይመስላችኋል

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት ።**

## ማጠቃለያ

ሕጉ በዋናነት የሚያመለክተው የሙሴን ሕግ ሲሆን ትክክለኛው ባሕርይ እንዲኖር የሚናገሩትን ፣ ነገር ግን ሕይወት የማይሰጡትንና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የሚያስችል ኃይል የሌላቸውን ትእዛዛት ያሳያል ። ብሉይ ኪዳን ወደ ድነት የሚያደርስ መንገድ በመሆን ይሰጠው የነበረው አገልግሎት በመስቀል ላይ ተጠርቆ ተወገደ ፣እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል በመንፈሱ የተሻለውን ኪዳን መሠረተ ። አዲስ ኪዳን በሕግ ሳይሆን በክርስቶስ ሆነ ! ነፃ ላወጣን ጌታ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብርና ምስጋና ይሁን ። አሜን !

## የቃል ጥቅስ

" በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው። " ቆላስይስ 2:14

″ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፥ አካሉ ግን **የክርስቶስ** ነው ። " ቆላስይስ 2:17

## ጥናት 8

### በመላዕክት ሳይሆን በክርስቶስ /Not Mysticism , But Christ/

### የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 2:18-23

**መግቢያ:**ባለፈው ጥናት በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ከነሕግጋቱ ክርስቶስ እንደደመሰሰውና እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ በማስወገድ ነፃ እንዳወጣን ሐ.ጳውሎስ ያስረዳበትን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ልዑል ና ምሉእ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ቦታ 'ለመላእክት አምልኮ, እንዲሰጥ ሐሰተኞች የሚያስተምሩትን ሐ.ጳውሎስ እንዲህ ዓይነቱ አምልኮ እንዳይፈጸም ያሰጠነቀቀበትን ምክር በዝርዝር እንዳስሳለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች:**

1. ***በቁ. 18"*** ትሕትናንና **የመላእክትን አምልኮ እየወደደ፥** ባላየውም **ያለ ፈቃድ እየገባ፥ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ** …ይላል። የመላእክትን አምልኮ የሚወድ ሰው ባሕርይ ምን ዓይነት ነው ?
2. ***በቁ. 19"*** እንደዚህ ያለ ሰው ራስ ወደሚሆነው አይጠጋም፥ ." ይላል። ራስ የተባለው ማነው?

   *20 -21* ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ፥

   *22* እንደ ሰው ሥርዓትና ትምህርት። **አትያዝ፥ አትቅመስ፥ አትንካ** ለሚሉት ትእዛዛት በዓለም እንደምትኖሩ ስለ ምን ትገዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋልና።

   *23* ይህ እንደ ገዛ ፈቃድህ በማምለክና በትሕትና ሥጋንም በመጨቆን ጥበብ ያለው ይመስላል፥ ነገር ግን ሥጋ ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ምንም አይጠቅምም ።

3. ከቁ22-23 ባለው ክፍል ለምንም አይጠቅምም የተባሉትን የሰው ሥርዓትና ትምህርቶችን በመዘርዘር ግልጽ ባልሆኑት ላይ ተወያዩ ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

4. ከክርስቶስ ጋር እንደ ሞተ ሰው በየእለቱ ሕይወታችን እኛ እየተገዛን ያለነው ለማነው ?
5. የመላዕክትን አምልኮ ለሚወዱና ከክርስቶስ ይልቅ የሰው ስርዓትና ወግ ለመጠበቅ ለሚጨነቁ ቤተሰቦቻችን እና ማኅበረሰባችን የኛ ኃላፊነት ምንድር ነው ?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ብቸኛ አስታራቂ አይደለም የሚለው እምነት ፣የመላእክት አምልኮንና የሞቱ ቅዱሳንን ጠባቂና አማላጅ አድርጎ በመቁጠር ለእነርሱ በሚደረገው አምልኮና በሚቀርበው ጸሎት ልምምድ ዛሬም ሲገለጽ ይታያል ። እንዲህ ዐይነቱ ልምምድ የክርስቶስን የበላይነትና የእግዚአሔር የመቤዠት ዕቅድ ውስጥ ያለውን ማዕከላዊነት ዋጋ ያሳጣል ። ለእግዚአብሔር አብ፣ ለእግዚአብሔር ወልድና ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ለመላእክት ወይም ለሰው የሚደረግ አምልኮና የሚቀርብ ልመና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስላልሆነ ሊወገድ ይገባዋል ።

**የቃል ጥቅስ**

" ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ፥ ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ፥ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ። " ቆላስይስ 2:18

## **ጥናት ፱**

## **በላይ ያለውን እሹ /Practice of Christ -Mind Set Up/**

### **የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ ፫:፩-፬**

**መግቢያ:**ባለፈው ጥናት ልዑል ና ምሉእ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ቦታ 'ለመላእክት አምልኮ, እንዲሰጥ ሐሰተኞች የሚያስተምሩትን ሐ.ጳውሎስ እንዲህ ዓይነቱ አምልኮ እንዳይፈጸም ያሰጠነቀቀበትን ምክር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሕይወታችን ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ስለሆነ ልባችን በዚያ ላይ ያረፈና አስተሳሰባችንም ሁሉ ከላይ ባሉ ነገሮች የተገዛ መሆን እንደሚገባው ሐ.ጳውሎስ የመከረበትን ሐሳቦች እንዳስሳለን ።

**ዓውደ ምንባባችን:**

**ከቁ 3-4** **ክርስቶስ ተኮር ሕይወት ማለት ......?**

- **ክርስቶስ** በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት **በላይ** ያለውን እሹ ። **በላይ ያለውን እሹ .....?**
- **በላይ** ያለውን **አስቡ** እንጂ **በምድር** ያለውን አይደለም ።**በላይ ያለውን አስቡ......?**
- **ሕይወታችሁም** በእግዚአብሔር **ከክርስቶስ** ጋር ተሰውሮአልና ።**ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና** ?
- **ክርስቶስ** በሚገለጥበት ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር **በክብር** ትገለጣላችሁ። **በክብር ትገለጣላችሁ** ?

**ጥያቄ 1**: ከላይ በእያንዳንዱ ቁጥር ላይ የተገለጹት ሐሳቦች ምን ማለት እንደሆኑ የተረዳችሁትን በዝርዝር ተወያዩ ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

**ጥያቄ 2:** በመሻቶቻችን ፣በአስተሳሰባችንና በአጠቃላይ በየዕለቱ ሕይወታችን ክርስቶስ ላይ እንዳናተኩር ተግዳሮት ከሚሆኑብን ነገሮች ጥቂቶቹን አጋሩ ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት ።**

**ማጠቃለያ**

በሕይወታችን ለማንኛውም ነገር ዋጋ፣ ግምትና ፍርድ የምንሰጠው ከዘላለማዊና ከሰማያዊ እይታ አንጻር መሆን አለበት። የየዕለት ግቦቻችንና ክትትላችን መንፈሳዊ ነገሮችን ለመሻት፣ ኀጢአትን ለመቃወም፣እንዲሁም የክርስቶስን ባሕርይ ለመላበስ ሊሆን ይገባል ። መንፈሳዊ ጸጋዎች፣ኃይል፣ ልምምዶችና በረከቶች ሁሉ የሚገኙት በክርስቶስ ዘንድ በሰማይ ነው ።

**የቃል ጥቅስ**

" በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም ። "ቆላስይስ 3:2

## **ጥናት 10**

### **አሮጌውን አውልቁ /Putting off Old Nature/**

### **የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 3:5-9**

**መግቢያ**: ባለፈው ጥናት ሕይወታችን ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ስለሆነ ልባችን በዚያ ላይ ያረፈና አስተሳሰባችንም ሁሉ ከላይ ባሉ ነገሮች የተገዛ መሆን እንደሚገባው ሐ.ጳውሎስ የመከረበትን ሐሳቦች ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የአሮጌውን **ሰው** ወይም **ማንነት** መገለጫ የሆኑ ስጋዊ ባሕርያትን አውልቁ ወይም አስወግዱ ብሎ የመከረበትን ሐሳቦች እንዳስሳለን።

### **የመወያያ ጥያቄዎች:**

### **የአሮጌው ሰው መገለጫ ባሕርያት:**

**1**.እንግዲህ በምድር ያሉቱን **ብልቶቻችሁን ግደሉ**፥ ሲል ምን ማለቱ ነው ?

2. ከዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣኦትንም ማምለክ ከሆነ መጎምጀት እንዴት ማምለጥ ይቻላል ?

**3**. ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ስድብንና የሚያሳፍርንም ንግግርን እንዴት ማስወገድ ይቻላል ?

**4**. የአሮገውን ሰው ሥራ ገፈው የጣሉ አማኞች እርስ በርስ ውሸትን የማይነጋገሩት ለምን ይመስላችኋል ?

### **ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

**5.** አሁን የተዋችኋቸው ነገር ግን ቀድሞ ትመላለሱባቸው ከነበሩት የአሮጌው ሰው መገለጫ ባህርያት ውስ ጥ ጥቂቶቹን አጋሩ ።

**6.** ዛሬስ በእግዚአብሔር ፊት ታማኝ ሆነን ራሳችንን መመርመር ብንችል የየትኛው አሮጌ ማንነት ተጠቂዎች ሆነን እንገኝ ይሆን ?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

### **ማጠቃለያ**

*አሮጌውን ማንነት ታግለን ማሸነፍ አለብን ። ካልሆነ ግን ሐ.ጳውሎስ እየሰጠን ያለው ማስጠንቀቂያ* በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሔር ቍጣ **በማይታዘዙ ልጆች** ላይ ይመጣል ነው ።

ጌታ ከፍርዱ ያድነን ። አሜን !

### **የቃል ጥቅስ**

"…. አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥" "ቆላስይስ 3:9

## ጥናት 11

## አዲሱን ልበሱ /Putting on The New Nature/

## የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 3:10-14

**መግቢያ**:ባለፈው ጥናት ሐ.ጳውሎስ የአሮጌውን **ሰው** ወይም **ማንነት** መገለጫ የሆኑ ስጋዊ ባሕርያትን አውልቁ ወይም አስወግዱ ብሎ የመከረበትን ሐሳቦች ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የዛ ተቃራኒ የሆነውን የአዲሱን **ሰው** ወይም **ማንነት** መገለጫ የሆኑ መንፈሳዊ ባሕርያትን ልብሱ ብሎ የመከረበትን ሐሳቦች እንዳስሳለን ።

## የመወያያ ጥያቄዎች:

### የአዲሱ ሰው መገለጫ ባሕርያት:

1. ***በቁ 10*** "የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት **የሚታደሰውን አዲሱን ሰው** ለብሳችሁታል።"የሚለውን አብራሩ።
2. ***በቁ 11*** "በዚያም **የግሪክ ሰው** አይሁዳዊም የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም" ይላል ። ልዩነቶቹ በምን ላይ እንደተመሰረቱ አብራሩ ። እነዚህን ሁሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች እኩል የሚያደርጋቸው ማነው ?
3. ከቁ 12-13 :እነዚህን ልበሱ ተብለው ከታች የተጠቀሱትን የአዲሱን ሰው ባሕርያቶች እያንዳንዳቸው በተግባር ምን ማለት እንደሆኑ አብራሩ ።

   *12* እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች **ቅዱሳን** ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ **ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ትህትናን፥ የዋህነትን፥ትዕግሥትን ልበሱ**። *13* እርስ በርሳችሁ **ትዕግሥትን** አድርጉ፥ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ **ይቅር** ተባባሉ። ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ **እንዲሁ አድርጉ።**

4. ***በቁ 14*** *ላይ እንደምንመለከተው " በእነዚህ ሁሉ ላይ ሁሉን በፍጹም አንድነት የሚያስተሳስረው እንዲለብሱት የተፈለገው የአዲሱ ሰው ባሕርይ ምንድር ነው። ትንሽ አብራሩት ።*

## ከሕይወት ጋር ማዛመድ

**5.** ይቅርታን የመቀበልና የማድረግ ተግዳሮቶቻችንን በምን እንደምናሸንፋቸው ለቡድናችሁ አጋሩ።

6. አይሁድ ፣ግሪክ ፣ ባሪያ ጨዋ ወዘተ ከመሰሰሉት የአሮገው ሰው መገለጫዎች ማርከሻ መድኃኒቱ ሁሉን ሰው እኩል ያደረገው ክርስቶስ መሆኑ ገብቶን በሕይወታችን ምን ያህል በሙላት ለብሰነዋል ?

- ❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

## ማጠቃለያ

በመንፈሳዊ ሕይወት የእድገት ጎዳና ላይ የአሮጌውን ሰው ማንነት ባሕርርያትን ማውለቅ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ያክል የአዲሱን ሰው ማንነት መገለጫ ባሕርያትን መላበስ ግን እጅግ በጣም አስፈላጊው ነገር ነው ። አሮጌ ልብሱን ያወለወቀ ሰው አዲሱን ልብስ ካልለበሰ እንግዲህ ራቁቱን መሆኑ አይደል ?

## የቃል ጥቅስ

"የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን **አዲሱን ሰው** ለብሳችሁታል። " ቆላስይስ 3:10

## <u>ጥናት 12</u>

## የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት

## Do all innthe name of the Lord Jesus !

### <u>የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 3:15-17</u>

**<u>መግቢያ:</u>** ባለፈው ጥናት የአዲሱን ሰው ወይም ማንነት መገለጫ የሆኑ መንፈሳዊ ባሕርያትን ልብሱ ብሎ ሐ.ጳውሎስ የመከረበትን ሐሳቦች ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የቆላስይስ አማኞች ወደ ውስጣቸው በልባቸው ሊነግስ ስለሚገባው ሰላም፣ ከላይ ያለውን እግዚአብሔርን ለማክበርና ወደ ጎን ደግሞ ከቅዱሳን ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት **<u>የሚያደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም</u>** ማድረግ እንደሚገባቸው ሐ.ጳውሎስ ያቀረበላቸውን ምክር እንዳስሳለን ።

### <u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. ***በቁ 15 " እንደ*** በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ **<u>ሰላም</u>** በልባችሁ ይግዛ ። የ**ምታመሰግኑም** ሁኑ "ይላል ። የልብ ሰላም ሙላትና የአስጋኝነት ሕይወት እንዴት የሚገናኙ ይመስላችኋል ?
2. ***በቁ. 16 "*** **<u>የእግዚአብሔር ቃል</u>** በሙላት ይኑርባችሁ " ማለት ምን ማለት ነው? ይህ እንዲሆን ምን ማድረግ የሚገባ ይመስላችኋል?
3. በጥበብ ሁሉ **<u>እርስ በርሳችሁ</u>** አስተምሩና ገሥጹ ። በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው **<u>በልባችሁ</u>** ለእግዚአብሔር ዘምሩ ። ከሚለው **<u>እርስ በርሳችሁ</u>** እና **<u>በልባችሁ</u>** በሚሉት ስር ተለይተው የተጠቀሱትን መንፈሳዊ ልምምዶች በመዘርዘር ተወያዩባቸው ።

### <u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>

4. ***በቁ.17*** "እግዚአብሔር አብን **በእርሱ እያመሰገናችሁ፥ በቃል** ቢሆን <u>ወይም</u> **በሥራ** የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ **<u>በኢየሱስ ስም</u>** አድርጉት ። " የሚለውን ቃል በየዕለቱ የሕይወት ውሳኔዎቻችን ምን ያህል እንደምንለማመደው ተሞክሮአችሁን ለቡድናችሁ አጋሩ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

### <u>ማጠቃለያ</u>

በየዕለት የሕይወት ውሳኔዎቻችን በምናስበው፣ በምንናገረውና በምናደርገው መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ መርሖች ስለሚሰጥ በማንኛውም ነገር ወደ እርምጃ ከመግባታችን በፊት የሚከተሉትን መጠየቅ ጠቃሚ ነው : (1)የሚደረገው ነገር ለእግዚአብሔር ክብር ሊሆን ይችላልን ? (2) የሚደረገው ነገር በጌታ በኢየሱስ ስም ሊከናወን ይችላልን ? (3) ለእግዚአብሔር ከልብ የሆነ ምስጋና በማቅረብ ሊደረግ የሚችል ነውን (4) የክርስቶስን ምሳሌነት በመከተል የሚደረግ ነውን (5) የሌሎችን ጽኑ እምነት ያዳክም ይሆን ? (6) ለእግዚአብሔር ቃል ያለኝን ጥማት ና የጽሎት ትጋት የሚቀንስ ይሆን ? (7) ስለ ክርስ ቶስ የምሰጠውን ምስክርነት ያዳክምኝ ይሆን ? ወዘተ. ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባናል ።

### <u>የቃል ጥቅስ</u>

" እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ፥ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት ።ቆላስይስ 3:16

## <u>ጥናት 13</u>

### ክርስቲያናዊ ቤተሰብ / The Christian Home/

### <u>የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 3:18-21</u>

<u>**መግቢያ:**</u> ባለፈው ጥናት የቆላስይስ አማኞች ወደ ውስጣቸው በልባቸው ሊነግስ ስለሚገባው ሰላም፣ ከላይ ያለውን እግዚአብሔርን ለማክበርና ወደ ጎን ደግሞ ከቅዱሳን ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት <u>**የሚያደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም**</u> ማድረግ እንደሚገባቸው ሐ.ጳውሎስ ያቀረበላቸውን ምክር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ <u>ክርስቲያናዊ ቤተሰብ</u> ምን መምሰል እንዳለበት ያቀረበውን ምክር እናያለን ።

<u>**ዐውደ ምንባባችንና ጥያቄዎቻችን:**</u>

*18* <u>**ሚስቶች ሆይ፥**</u> በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ **ተገዙ**። ......**ተገዙ**

<u>*19* **ባሎች ሆይ፥**</u> ሚስቶቻችሁን <u>**ውደዱ መራራም**</u> አትሁኑባቸው።.......<u>**ውደዱ መራራም ?**</u>

*20* <u>**ልጆች ሆይ፥**</u> ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ። ...**ታዘዙ ?**

*21* <u>**አባቶች ሆይ፥**</u> ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው ።....**አታበሳጩአቸው ?**

<u>**ጥያቄ1:**</u> ከላይ በምትመለከቱት መሰረት ለሁሉም ክርስቲያን የቤተሰብ አባል ተለይቶ የተሰጠውን ኃላፊነት በመዘርዘር እያንዳንዳቸው ምን ማለት እንደሆኑ በተቀመጡበት ቅደም ተከተል ተራ በተራ አብራሩ ።

<u>**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**</u>

<u>**ጥያቄ 2**</u>: እኛ በምንገኝበት ድኅረ ዘመናዊነት ዓለም <u>**የትዳርን ትርጉምና**</u> <u>**የቤተሰብን መስተጋብር**</u> አስመልክቶ በምንኖርባት አሜሪካም ይሁን በሌሎች አገሮች ያሉ ተግዳሮቶችን **በአጠቃላይ መልኩ** ለአብነት እየጠቀሳችሁ ተወያዩ ።

<u>**ጥያቄ 3**</u>: እኛ በምንገኝበት በዚህ ድኅረ ዘመናዊነት ዓለም የትዳርን ትርጉምና የቤተሰብን መስተጋብር አስመልክቶ ከእግዚአብሔር በተፃራሪነት <u>**ክርስቲያናዊ ቤተሰብን**</u> በተለየ ሁኔታ እየተፈታተኑ ያሉ ተግዳሮቶችን ለአብነት እየጠቀሳችሁ ተወያዩ ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

<u>**ማጠቃለያ:**</u>

በክርስቲያናዊ ቤተሰብ መስተጋብር ውስጥ :<u>**ሚስት**</u> ለባልዋ በመታዘዝ አክብሮትንና ፍቅርን ምቹ ረዳት መሆንሆና በመልካም እናትነት ጥሩ የቤተሰብ አያያዝ ሚናን መወጣት ሲጠበቅባት በሌላው አንፃር <u>**ባል**</u> ደግሞ በቤተሰቡ ያለውን መሪነት በጨዋነት፣ በአክብሮትና በኃላፊነት ስሜት ተግባራዊ ለማድረግ ቢያንስ የሚከተሉት ይሦስት ወሳኝ ኃላፊነቶች ይጠበቁበታልል። እነዚህም:

**(1)** ለሚስቱ ፍቅርን በመስጠት ለደህንነቷ ጥበቃና እንክብካቤን ማድረግ **(2)** ሚስቱን ማክበር ፣ማድነቅና ጨዋዊ ተግባቦትን ማበልጸግና ስለ እርሷ ተቆርቋሪና ግድ የሚለው **(3)** አቅሙ በፈቀደው ሁሉ ለቤተሰቡ መንፈሳዊና ስጋዊ አቅርቦቶችን ለማሟላት ጥረት ማድረግ አለበት የሚሉት ናቸው ። <u>**ልጆች**</u> ደግሞ የወላጆቻቸውን ፈለግ የመከተል ዕድላቸው ከፍተኛ ነው ። ትዳራችንን እንደቃሉ እንድንመራው ጌታ ይርዳን ።

<u>**የቃል ጥቅስ**</u>

“ ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ። ” ኤፌ 5:33

## ጥናት 14

### ክርስቲያን በስራ ቦታ/Christian at Workplace/

### የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 3:22-4:1

**መግቢያ:**ባለፈው ጥናት ክርስቲያናዊ ቤተሰብ ምን መምሰል እንዳለበት ሐ.ጳውሎስ የቈላስይስ አማኞች ያቀረበውን ምክር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ክርስቲያኖች በስራ ቦታቸው የሚያደርጉትን ሁሉ ጌታን ለማገልገል እንደሚያደርጉት ቆጥረው በታማኝነት እንዲሰሩ አጥብቆ የሰጣቸውን ምክር እንቃኛለን ።

**ዐውደ ምንባባችንና ጥያቄዎቻችን:**

**ከቁ.22-25** ባለው ክፍል እንደ ተዘርዝሮ እንደምናነበው በሐ.ዻውሎስ ምክር መሠረት የዛን ዘመን ባሮች/አገልጋዮች በሥራ ቦታቸው እንደ አንድ ክርስቲታን እንዲያሚሉ የሚጠበቅባቸው የስራ ሥነ-ምግባር እንደሚከተለው ነበር ።

**ባሪያዎች ሆይ፥**

1. በቅን ልብ
2. ጌታን በመፍራት
3. ለታይታ ባለመገዛት
4. በሁሉ መታዘዝ
5. በትጋት ማገልገል

**ጥያቄ** 1: እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች አሟልተው የሚያገለግሉ ባሮች ብድራታቸውን ከማን ሊቀበሉ እንደሚችሉ ነው ታውቃላችሁ ያላቸው ?

**ጥያቄ 2**: ባሮቹ እያገለገሉ የነበረው የምድር ጌቶቻቸውን ሆኖ ሳለ ሐ.ጳውሎስ ግን የምታገለግሉት **ጌታ ክርስቶስን ነ**ው ያለበት ምክን ያት ለምን ይመስላችኋል ?

**4:1 ጌቶች ሆይ:**

**1**. ጌታ እንዳላችሁ አውቃችሁ **2**. በጽድቅ ና **3**. በቅንነት አድርጉላቸው ።

**ጥያቄ 3:** ለጌቶች ለአሠሪዎች የተሰጣቸው ምክረ ቃሎች ምን ማለት እንደሆኑ አብራሩ።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

**ጥያቄ 4:** በስራችን ቦታ የምናደርገው ትጋትና ታማኝነት እንዲሁም ከሌሎች ጋር ተግባብቶና ተከባብሮ በመስራት የምናሳየው ምሳሌነት በክርስትና ላይ ምን ዓይነት መልካም ተፅፅኖ ሊያመጣ እንደሚችል ተሞክሮአችሁን ለቡድናችሁ አጋሩ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ:**

ክርስቲያኖችን ጌታ በሠራተኛነት ባስቀመጣቸው ስፍራ በቅንነት፣ጌታን በመፍራት፣ ለታይታ ባለመገዛት/ በታማኝነት ፣ ኃትጢአት ባልሆነ ነገር በሁሉ በመታዘዝ አሠሪዎቻቸውን ማገልገል እንዳለባቸው ሲመክር በሌላው አንፃር አሰሪዎች ደግሞ ከእነሱ የሚበልጥ ጌታ በሰማይ እንዳላቸው አውቀው በጽድቅና በቅንነት ለሰራተኞቻቸው የሚገባቸውን እንዲያደርጉላቸው ያሳስባል ። ምክንያቱም ቃሉ " **የሚበድልም የበደለውን በብድራት ይቀበላል፥** ለሰው ፊትም አድልዎ የለም ። "ይላልና !

**የቃል ጥቅስ:**

"**ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፥ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት**" ቆላስይስ 3:23

## <u>ጥናት 15</u>

## ክርስቲያን በዓለም/ Christian in the World/

## <u>የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 4:2-6</u>

**መግቢያ:**ባለፈው ጥናት ክርስቲያኖች በስራ በታቸው የሚያደርጉትን ሁሉ ጌታን ለማገልገል እንደሚያደርጉት ቆጥረው በታማኝነት እንዲሰሩ ሐ.ጳውሎስ ለቈላስይስ አማኞች የሰጣቸውን ምክር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ክርስቲያኖች በዓለም ላይ እንዴት መመላለስ እንደሚገባቸው ያቀረበላቸውን ምክር እንቃኛለን ።

### <u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. በቁ2. "ከ**ማመስገን** ጋር <u>**በጸሎት**</u> <u>**እየነቃች**</u>ሁ ለእርሱ <u>**ትጉ**</u> ። " ለጸሎት ምናስጋና፣ ትጋትና ንቃት የሚያስፈልጉት ለን ይመስላችኋል ?
2. **በቁ*3-"*** በዚያን ጊዜም ስለ እርሱ ደግሞ <u>**የታሰርሁበትን የክርስቶስን**</u> **ምሥጢ**ር እንድንነግር እግዚአብሔር **የቃሉን ደጅ ይከፍትልን** ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ ። " <u>**የክርስቶስን**</u> <u>**ምሥጢ**ር ምንድር ነው ?</u> **የቃሉን** <u>**ደጅ ይከፍትልኝ**</u> ዘንድ ማለትስ ምን ማለት ነው ?
3. **በቁ*4"*** <u>**ልናገር እንደሚገባኝ**</u> ያህል እገልጠው ዘንድ <u>**ጸልዩልኝ። ሲል**</u> ሐ ጳውሎስን ያሳሰበው በአካሉ እስረኛ መሆኑ ሳይሆን የታሰረበትን ዓላማ በብቃት መፈጸም ይችል ዘንድ እንዲጸልዩለት መጠየቁ ስለ እርሱ የወንጌል ሸክም ምን ያመለክታል ?
4. **በቁ*5"*** ዘመኑን እየዋጃችሁ፥ <u>**በውጭ ባሉቱ ዘንድ**</u> በ**ጥበብ** ተመላለሱ"ይላል። ዘመን መዋጀት ማለት ምን ማለት ነው?
   በውጭ ያሉቱ እነ ማናቸው ? በጥበብ መመላለስ ማለትስ ምን ማለት ነው?
5. **በቁ*6*** ***"***<u>**ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ**</u> እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ፥ በጨው እንደ ተቀመመ፥<u>**በጸጋ**</u> ይሁን"ይላል ለውጤታማ ተግባቦት <u>**እውቀትና ጸጋ**</u> ያስፈለጉበት ምክንያት ለምን ይመስላችኋል ?

### <u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>

6. ሐ.ጳውሎስ እስር ቤት ሆኖ እንኳ ስለወንጌል እንድገደደው ሁሉ እኛስ ይህን አደራ ምን ያህል እየተወጣነው ነው ?
7. <u>*በማያምኑት ዘንድ በሕይወት አካሄዳችን ከንግ ግራችን ጀምሮ ምን ያህል እንጠነቀቃለን ?*</u>

- ❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

### <u>ማጠቃለያ:</u>

ሐ.ጳውሎስ እስር ቤት ሆኖ እንኳ ስለወንጌል እንድገደደው ሁሉ እኛም ይህን አደራ አለብንና እንዲሁ ሊገደን ይገባል ። ዘመኑን እየዋጀን በጥበብ እየተመላለስን ለንግግራችን እውቀትና ጸጋን በጸሎትከ ጌታ እየጠየቅን በውጭ ላሉት ክርስቶስን በሕይወታችን ልንገልጥላቸው ይገባል ።

### <u>የቃል ጥቅስ</u>

"ዘመኑን እየዋጃችሁ፥ <u>**በውጭ ባሉቱ ዘንድ**</u> በጥበብ ተመላለሱ ። " ቆላስይስ 4:5

## **ጥናት 16**

### **ማጠቃለያና የስንብት ቡራኬ/ Closing Exhortations & Blessings/**

### **የምንባብ ክፍል: ቆላስይስ 4:7-18**

**መግቢያ**:ባለፈው ጥናት ክርስቲያኖች በዓለም ላይ እንዴት መመላለስ እንደሚገባቸው ያቀረበላቸውን ምክር ለቈላስይስ አማኞች የሰጣቸውን ምክር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው የመጨረሻ ጥናታችን ደግሞ የመልዕክቱን የመዝጊያ ሰላምታ እንዳቃኛለን ።

## **ዐውደ ምንባባችን :**

*"7* **የተወደደ ወንድምና የታመነ አገልጋይ** በጌታም አብሮኝ ባሪያ የሆነ **ቲኪቆስ** **ኑሮዬን** ሁሉ ያስታውቃችኋል።

*8 -9* ወሬያችንን እንድታውቁና **ልባችሁን እንዲያጽናና፥** ከእናንተ ከሆነውና **ከታመነው ከተወደደውም ወንድም** **ከአናሲሞስ** ጋር ወደ እናንተ የምልከው ስለዚህ ምክንያት ነው። የዚህን ስፍራ ወሬ ሁሉ ያስታውቁአችኋል ።

*10 - 11* ከተገረዙት ወገን ያሉት፥ **አብሮ ከእኔ ጋር የታሰረ** **አርስጥሮኮስ** የበርናባስም የወንድሙ ልጅ **ማርቆስኢዮስጦስም** የተባለ ኢያሱ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። ስለ **ማርቆስ**። ወደ እናንተ ቢመጣ፥ **ተቀበሉት** የሚል ትእዛዝ ተቀበላችሁ። **በእግዚአብሔር መንግሥት ከእኔ ጋር አብረው የሚሠሩት** እነዚህ ብቻ ናቸው፥ **እኔንም አጽናንተውኛል**።

*12* ከእናንተ የሆነ **የክርስቶስ ባሪያ** **ኤጳፍራ** ሰላምታ ያቀርብላችኋል። በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ተረድታችሁና

**ፍጹማን ሆናችሁ እንድትቆሙ፥** ሁልጊዜ **ስለ እናንተ** **በጸሎቱ ይጋደላል።**

*13* ስለ እናንተ በሎዶቅያም በኢያራ ከተማም ስላሉቱ እጅግ እንዲቀና እመሰክርለታለሁና።

*14* የተወደደው **ባለመድኃኒቱ** **ሉቃስ** **ዴማስም** ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።

*15* በሎዶቅያ ላሉቱ ወንድሞችና **ለንምፉን** **በቤቱም ላለች ቤተ ክርስቲያን** ሰላምታ አቅርቡልን።

*16* **ይህችም መልእክት በእናንተ ዘንድ ከተነበበች በኋላ፥ በሎዶቅያ ሰዎች ማኅበር ደግሞ እንድትነበብ አድርጉ። ከሎዶቅያም የምትገኘውን መልእክት እናንተ ደግሞ አንብቡ።**

*17* **ለአክሪጳም**። **በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽሙው ተጠንቀቅ በሉልኝ።**

*18* **በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ ነው። እስራቴን አስቡ። ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።**

**ጥያቄ1:** ሐ. ጳውሎስ በደብዳቤው የመዝጊያ ሰላምታ ቢያንስ የአሥር አገልጋዮችን ስም ጠቅሷል፣ እያንዳንዳቸውን የገለጠበትና ባሕርይ አብራሩ ።

**ጥያቄ2: "** ሐ. ጳውሎስ **እኔንም አጽናንተውኛል** "ሲል ይነበባል።እነ ማናቸው ያጽናኑት? እንዴትስ ጳውሎስን የሚያክልትላቅ አገልጋዩ በእነርሱ ሊጽናና የፈቀደ ይመስላችኋል ?

**ጥያቄ3:** ይህን ደብዳቤ ለቆላስይስ አማኞች ከተነበበላቸው በኋላ ለሎዶቅያ ማህበር እንዲነበብ ማዘዙ ምንን ያመለክታል ?

**ጥያቄ4:** ሐ. ጳውሎስ " **እስራቴን አስቡ** ። ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል ?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

**ጥያቄ5**: ዛሬ ባጠናቀቅነው የሐ.ጳውሎስ መልዕክት የመዝጊያ ሰላምታ ልባችሁ እጅግ የተነካበት ሐሳብ ካለ ለቡድናችሁ አካፍሉ ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ:**

"በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽሙው ተጠንቀቅ በሉልኝ ። ይህ መልዕክት ለእኛም ዛሬ ህያው ነው ። አሜን !

**የቃል ጥቅስ**

""በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ ነው። እስራቴን አስቡ። ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።" ቆላስይስ 4:18

# ክፍል ሁለት

## የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ለጢሞቴዎስ

# አንደኛ

**መግቢያ**

**ጸሓፊው ጳውሎስ**:

በመልእክቱ መግቢያ ላይ ፀሀፊው የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ ከሆነዉ ከጳውሎስ (1ጢሞ 1፡1) በማለት እራሱን በትክክል ስላስተዋወቀ የፀሀፊውን ማንነት በግልፅ ሐዋርያው ጳውሎስ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

**መልዕክቱ የተፃፈበት ዘመን**

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን መልዕክት ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ሮም እስር ቤት ከመወሰዱ ቀደም ብሎ ከ 63-65 ዓ.ምመካከል ባሉት ግዚያት ዉስጥ እንደፃፈው ይታመናል ።

**ተደራስያኑ**

"በእምነት እውነተኛ ልጇ ለሆነው ለጢሞቴዎስ" (1ጢሞ 1፡2)

ሐዋርያው ጳውሎስ በ52 ዓ.ም ገደማ ልስጥራን ወደምትባለዉ በአሁኗ ቱርክ ዉስጥ ወደምትገኝ አንድት ከተማ ለአገልግሎት በተጓዘበት ወቅት በዚያ ይኖር የነበረዉንና በወቅቱ በጣም ወጣት ልጅ የነበረውን ጢሞቴዎስን ለመጀመሪያግዜ አገኘው። ጢሞቴዎስ አባቱ ግሪካዊ ስሆን እናቱ ግን አይሁዳዊ ክርስቲያን ነበረች። በዚህም ምክንያት ይበልጥ የእናቱ የእምንት ተፅዕኖ የነበረበትና የብሉይ ኪዳን መፅሀፍት የሚያውቅ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር የሆነ ወጣት ነበር (ሐዋ 16፡1፣ 2ጢሞ 1፡5)። በዚያም ጳውሎስ ስለዝሀ ወጣት ከሰማዉ መልካም ምስክርነት የተነሳ ከእርሱ ጋር ይዞት ሊሔድ ወደደ (ሐዋ 16፡2-4) ከዚህ ግዜ ጀምሮ ጢሞቴዎስ የጳውሎስ መንፈሳዊ ልጅ በመሆን ለረጅም ግዜ ጳውሎስን በሔደበት እየተከተለ እንዳገለገልውና እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ መሆኑንም በተለያዩ ደብዳቤዎቹ ላይ ጳውሎስ ሲመሠክርለት እንመለከታለን (ፊል 2፡22)።

**የተፃፈበት ዓላማና ታሪካዊ ዳራ**

ጳውሎስ ይህን መልዕክት ከዚህ በፊት በኤፌሶን የምትገኘዋን ቤተ ክርስቲያን ከጢሞቴዎስ ጋር ለመጎብኘት በሔደ ጊዜ በወቅቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ የስህተት እና የሀሰት ትምህርቶች በመነሳታቸው ምክንያት የነበርው ሁኔታ አደገኛ ከመሆኑ የተነሳ ጢሞቴዎስን በዚያ እንዲቀርና ይህንን የስህተት አስተምሮት እውነተኛውን ወንጌል በማስተማር እንዲቃወም ሃላፊነት እንዴት ሰጥቶት እንደነበር በማስታወስ ይጀምራል (1ጢሞ1፡3-4)። ጢሞቴዎስ በእድሜ ወጣት ከመሆኑ የተነሳ በመሪነት ደረጃ ብዙ ልምድ የሌለው በመሆኑ በወቅቱ ከነበሩት የስሀተት ተምህሮቶች በተጨማሪ የተሰጠውን ሃላፊነት የሚገዳደሩ አንዳንድ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበሩ(1ጢሞ4፡12)።

1ኛ ጢሞቴዎስ ከሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መፃሀፍት ሁሉ በበለጠ ሁኔታ ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራርና ሃላፊነት በትኩረትየተፃፈ መልዕክት በውስጡ ይዟል።

ይህንን የቤተ ክርስቲያንና የጢሞቴዎስን ተግዳሮት የተረዳው ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ሊያደርጋቸውና ሊያስተምራቸው የሚገባውን ዋና ዋና ነገሮች በመልዕክቱ ይዳስሳል። በዚህም መልዕክቱ ውስጥ የሚከተሉት ሃሳቦች ይገኙበታል።

1. ከሃሰተኛ አስተማሪዎች እንዲጠነቀቅ (1ጢሞ 1:3-11 ፤ 4፡1-16)
2. እምነትና በጎ ህሊና እንዲኖረው (1ጢሞ 1፡19)
3. ቅዱሳን በኑሮአቸዉ እንዴት እግዚአብሔርን ማምለክ እንዳለባቸው እና በህብረት የአምልኮ

ግዜ ሊኖርስለሚገባው ስርዓት (1ጢም 2፡1-15)

4. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊኖራችው ስለሚገባ የህይወት ዘይቤ (1ጢሞ 3፡1-16)
5. ጢሞቴዎስ እራሱ በቤተ ክርስቲያ ውስጥ ያሉትን መበልቶች ፣ሽማግሌዎችና ባሪያዎችን በምን መልኩ ሊያገለግላቸው እንደሚገባ (1ጢሞ 5፡1 – 27)
6. የገንዘብ ፍቅር አደገኝነትን እና አገልጋዬች ከዚህ ለምን መሸሽ እንደሚባቸዉ ያስተምራል (1ጢሞ 6:1-19)።

**ጥናት 1**

**ከሐሰተኛ መምህራን መጠበቅ**

**የምንባብ ክፍል፡ 1ጢሞ1፡1-11**

**መግቢያ፡-** በዚህ በመልዕክቱ መግቢያ ላይ ሐዋሪያው ጳውሎስ መንፈሳዊ ልጁ ለነበረው ለጢሞቴዎስ በወቅቱ ጢሞቴዎስይመራት በነበረችው በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከነበሩት ከሀሰተኛ የህግ መምህራን እንዴት መጠንቀቅ እንዳለበት ሲያሳስበው እንመለከታለን፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ከዚህ ቀደም በኤፌሶን እንዲቀመጥ ለምን አዘዘው? ቁ 3–4
2. ጳወሎስ ከቁ 3–4 ባለዉ ክፍል ውስጥ "ልዩ ትምህርት" ብሎ የጠቀሰው ምን አይነት ትምህርት ይመስላችኋል?የዚህ አይነት ትምህርት ውጤቱ ምንድን ነው ? ተወያዩበት፡፡

3. ከ ቁ5–7 ላይ ባለው ሀሳብ መሰረት እነዚህ መምህራን እውነተኛ የሆነውን ወንጌል እንዲያስተምሩ ያደረጋቸውነገሮች ምንድን ናቸው?
4. ከ ቁ 8–11 ሐዋርያው ህግ የሚጠቅመው ለእነማን እንደሆነ ይናገራል? ይህ ሀሳብ ከእነዚህ ከሀሰተኛ የህግ መምህራን ጋር እንዴት ይገናኛል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

5.ዛሬስ እኛ እንደእነዚህ ካሉ ሀሰተኛ መምህራን እራሳችንን እንዴት መጠበቅ እንችላለን?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

ሀሰተኛ መምህራን በቤተ ከረስቲያን ታሪክ ውስጥ ሁሉ መልካቸውን በመቀያየር ለቤተክርስቲያንና ለቅዱሳን ህይወት እድገትእንቅፋት ሆነው እንደነበሩ ፣ እንዳሉ እና ወደፊትም እንደሚኖሩ በማወቅ እንደ ጢሞቴዎስ ያሉ የቤተ ከረስቲያን መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ እያንዳንዱ ምእመን ከእንደነዚህ ካሉ ስህተቶች ራሱን ሊጠብቅ ይገባል።

**የቃል ጥቅስ**

"እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮች ክርክርን ያመጣሉና በእምነት ግን ላለ ለእግዚአብሔር መጋቢነት አይጠቅሙም" 1ጢሞ 1:4

**ጥናት2**

**ለጳውሎስ የተሰጠዉ ጸጋ**

**የምንባብ ክፍል፡ 1ጢሞ 1፡12-20**

**መግቢያ፡-** ባለፈው ጥናታችን በየዘመናቱ መልካቸዉን እየቀያየሩ ከሚመጡ የሀሰት ትምህርቶች እንዴት እራሳችንን መጠበቅ እንደሚገባን ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ፤ ስለዳንበት ልዩ የእግዚአብሔር ጸጋ ምንነት ለጢሞቴዎስ ጳውሎስ የነገረዉን እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ የምንባብ ክፍል ዉስጥ ስለራሱ የሚናገረው ነገር ምንድን ነው? ቁ 13 እና 15 ይመልከቱ።
2. እንዲህ ላለው ሰዉ የተገለጠዉ ወይንም የተሰጠዉ የእግዚአብሔር ጸጋ ምን አይነት ነበር? ቁ 12-14
3. ጳውሎስ እንዲህ ያለዉ የእግዚአብሔር ጸጋ በእርሱ ላይ የተገለጠበት ምክንያት ምን እንደሆነ ነዉ የሚናገረዉ? ቁ 17

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

4. ጌታ ወደ ህይወታችሁ በመጣ ግዜ የነበራችሁ ህይወት ምን ይመስል ነበር? ከነበራችሁበት ከዚያ እናንተንለማዉጣት የተገለጠዉ የእግዚአብሔር ጸጋ ምን ያህል ይመስላችኋል? ተወያዩበት።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታ አይኖቹን ከፍቶለት ወደ እርሱ ከመምጣቱ በፊት የኖረዉን ሀይማኖታዊ ህይወቱን ሲያስበው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ ካልሆነ በስተቀር ፍፁም መዳን የሚገባው ሰው እንዳልነበረ ስለተረዳ የዚህ የእግዚአብሔር ታላቅጸጋ መገለጫ ምሳሌ ነኝ ይላል። ዛሬም እኛ እያንዳንዳችን የመጣንበትን ዘወር ብለን ስንመለከት ከጳውሎስ የተለየ ምስክርነት ስለመዳናችን ሊኖረን አይችልም።

**የቃል ጥቅስ**

“የጌታችንም ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ ካሉ ከእምነትና ከፍቅር ጋር አብልጦ በዛ” 1ጢሞ 1:14

S

## ጥናት 3

## የአምልኮ መመሪያ

## የምንባብ ክፍል፡ 1ጢሞ 2፡1-7 (ክፍል 1)

**መግቢያ፡-** ባለፈው ጥናታችን ሐዋርያው ጳውሎስ ከራሱ ህይወት በመነሳት ስለድነታችን የተገለጠዉ የእግዚአብሔር ጸጋ ምንነትና ጥልቀት ለጢሞቴዎስ የገለጠበትን ሀሳብ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ፤ አማኞች ለእግዚአብሔርየሚያቀርቡት አምልኮ ምን መምሰል እንዳለበት ጳውሎስ የሰጠዉን መመሪያ ክፍል አንድን እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ሐዋርያው ጳውሎስ ከሁሉ በፊት ቅዱሳን እንዲያደርጉት የሚመክረዉ ነገር ምንድን ነው?ቁ 1 ና 2 ይመልከቱ ።
2. በ ቁ 1 እና 2 ላይ በመጀመሪያ የግል ህይወታችንን በተመለከተ ቀጥሎም በዙሪያችን ያሉትን በሚመለከትልናደርገው ጳውሎስ የሚመክረንን ሀሳቦች በመለየት ተወያዩበት።
3. በ ቁ3 እና 4 ባለው ሀሳብ መሠረት ከላይ የተዘረዘሩት የህይውት ልምምዶች በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ደስየሚያሰኙ መሆናቸዉ ለምንድን ነው? እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ካለው ሀሳብ ጋርስ እንዴት ይገናኛል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

4.እግዚአብሔርን የመምሰል ህይወትና ለሌሎች የመማልድ አገልግሎት እግዚአብሔር የሚደሰትበት ነገር መሆኑን በመገንዘብ በህይወታችን ምን ያህል ተግባራዊ እያደረግን እንገኛለን?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

አማኞች የተጠራነው ጥሪ ከራሳችን ፍላጎት የወጣ እና የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ሀሳቡን ለሰዎች ሁሉ የሚማልድ አልፎም እርሱን የሚመስል ህይወትን በመኖር ሌሎችን ወደ ክርስቶስ እንድንማርክ እንደሆነ በመረዳት ይህንን ህይወት እንድንኖር እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

**የቃል ጥቅስ**

"ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው" 1ጢሞ 2:3-4

## <u>ጥናት 4</u>

## የአምልኮ መመሪያ

## <u>የምንባብ ክፍል፡ 1ጢሞ 2፡8-15 (ክፍል 2)</u>

**<u>መግቢያ፦</u>** ባለፈው በክፍል አንድ ጥናታችን አማኞች እንዴት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ የግልና እንዲሁም ሌሎችን ያቀፈ የፀሎትና የአምልኮ ህይውት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ካለፈው በመቀጠልጳውሎስ አማኞች ሊኖራቸው ስለሚገባ ስነ ምግባርና የአኗኗር ዘይቤ የሰጠዉን መመሪያ እንመለከታለን።

**<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>**

1. ከ ቁ 8-10 ባለዉ ሀሳብ መሰረት ወንዶችና ሴቶች እግዚአብሔር ሲያመልኩ ሊያደርጓቸዉ የሚገቡ ነገሮች ምንድንናችው?
2. በ ቁ 9-10 ላይ ሴቶች ብዙ ራሳቸውን በመሸለም እንዳይወጡ የሚያዛቸዉ ለምንድ ነዉ? ከ1ጢ 5:14 እናከ1ጴጥ 3:3-4 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
3. በ ቁ11 እና 12 መሠረት ሴት በዝግታ እንድትማር እንጂ እንዳታስተምር ጳውሎስ ያልፈቀደበት ምክንያት ምንድንይመስላችኋል? በኤፌሶን ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን አንጻር በመመልከት ተወያዩ ከሐዋ18: 24-26, ሮሜ 16:1,6,12
4. በዚህ ክፍል ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ በአደባባይ የሆነን የሴቶችን አገልግሎት ፈፅሞ የሚቃወም ይመስላችኋል?ለምን? ከሐዋ18: 24-26፤ ሮሜ 16:1,6,12 የተጠቀሱ ሴቶችንና አገልግሎታቸው በመመልከት ተወያዩ።

**<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>**

5.ውስጣዊ የሆነ ዉበት ከዉጭ ከሚታይ ማሸብረቅ ይልቅ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት እንዴት ይህንን በህይወታችን ልንተገብረዉ እንችላለን? ቆላ 3:17 ይመልከቱ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**<u>ማጠቃለያ</u>**

እግዚአብሔርን እንፈራለን የምንል አማኞች ሁሉ (ወንድም ይሁን ሴት) ሐዋርያው ጳውሎስ የውስጥ ማንነታችን በዉጭከሚታየው ማንነታችን ይበልጥ ሰዎችን ወድ ክርስቶስ የሚማርክ እንዲሆን በዚህ መልዕክቱ አጥብቆ ያሳስባል።

**<u>የቃል ጥቅስ</u>**

“እግዚአብሔርን እንፈራለን ለሚሉት ሴቶች እንደሚገባ፥ መልካም በማድረግ እንጂ በሽሩባና በወርቅ ወይም በዕንቍ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለሙ።” 1ጢሞ 2:10

## ጥናት 5
## የእረኞች መመዘኛ
## የምንባብ ክፍል፡ 1ጢሞ 3፡1-7

**<u>መግቢያ፦</u>** ባለፈው ጥናታችን ሐዋርያው ጳውሎስ አማኞች ሁሉ ውጫዊ ከሆነው ማንነታቸው ይልቅ የውስጥ ውበታቸው ሌሎችን ይበልጥ ሊስብ እንደሚገባ ያሳሰበውን ሀሳብ ተመልክተን ነበር፤ በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ለእረኝነት አገልግሎት የተሰጠዉን መመዘኛ በዝርዝር እንመለከታለን።

### <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በ ቁ 1 መሠረት የኤጲስ ቆጶስነት አገልግሎት መልካም ስራ ነው የተባለው ከምን አንፃር ይመስላችኋል? ኤጲስቆጶስ ማለትስ ምን ማለት ነው?
2. ከ ቁ 2-7 ለኤጲስ ቆጶስነት የተሰጡት መመዘኛዎች ምንድን ናቸው? በእያንዳንዱ መመዘኛ ላይ በዝርዝር ተወያዩ።
3. በ ቁ 4 ከተሰጡት መመዘኛዎች አንዱ ገንዘብን አለመውደድ ነው፤ ገንዘብን አለመውደድ እንዴ አንድ መመዘኛመቅረቡን እንዴት ትመለከታለህ?
4. አዲስ ክርስቲያን ለቤተ ክርስቲያን መሪነት መመረጥ የሌለበት ለምንድን ነው?

### <u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>

5. አሁን ባለንበት ዘመን ቤተ ክርስቲያን ችል ያለችው ወይም መልካም ምስክርነት መሆን ያቃታት ባህርይ የትኛው ይመስልኋል?

- ❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

### <u>ማጠቃለያ</u>

በቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም እረኛ ለመሆን ከዚህ ክፍል እንደምንረዳዉ ፍላጎት ብቻ በቂ አይደለም፤ ከፍላጎት በተጨማር የመሪ ህይወትና ባህሪ በቅዱሳንና በውጭ ባሉት ጭምር መልካም ምስክርነት ያለው ሊሆን የግድ ነዉ።

### <u>የቃል ጥቅስ</u>

“ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው።” 1ጢሞ 3፡1

## ጥናት 6

## የዲያቆናት መመዘኛ

## የምንባብ ክፍል ፡ 1ጢሞ 3፡8-16

**መግቢያ፡-** ባለፈው ጥናታችን አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የመሪነቱን ቦታ ከመፈለግ ባለፈ ህይወቱና ባህርይዉ በውስጥናበዉጭ ባሉት ሰዎች ሁሉ ዘንድ ያለነቀፋ ሊሆን እንደሚገባ ተመልክተን ነበር፤ በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ለ ዲያቆናት የተሰጠዉን መመዘኛ በዝርዝር እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ከ ቁ 8 -13 ለዲያቆናት በተሠጡት መመዘኛዎች ላይ በዝርዝር ተወያዩ።
2. በ ቁ 10 ላይ "አስቀድሞ ይፈተኑ" ብሎ ጳውሎስ ሲናገር መፈተናቸው ለምን አስፈለገ? የሚፈተኑትስ እንዴትነው?
3. ቁ 13 በመልካም ላገለገሉ ዲያቆናት የተሰጠዉ ተስፋ ምንድን ነው? ከማቴ 25:21 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
4. በቁ 14-15 ላይ ባለው ምንባብ መሰረት ይህንን መልዕክት ጳውሎስ የፃፌበት ዓላማ ምንድን ነው?
5. በቁ 16 እግዚአብሔርን የመምሰል ሚስጥር እንዴት ነዉ የተገለጠዉ? በዝርዝር ተወያዩበት።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. በየዕለት ኑሮህ / ሽ ያለ ነቀፋ ለመመላለስ ማድረግ ያለብህ / ሽ ነገሮች ምንድን ናቸው?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

አገልጋይ (በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑትን ሁሉ ማለት ነው) በነገር ሁሉ ታማኝና ያለነቀፋ መኖርን በመለማመድ በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት እንዴት ማገልገልና መኖር እንደሚገባ ማወቅ ይገባል ።

**የቃል ጥቅስ**

"እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፥ በመንፈስ የጸደቀ፥ ለመላእክት የታየ፥ በአሕዛብ የተሰበከ፥ በዓለም የታመነ፥ በክብር ያረገ።" 1ጢሞ 3:16

## ጥናት 7

## ለጢሞቴዎስ የተሰጠ መመሪያ

## (ክፍል አንድ)

## የምንባብ ክፍል፡ 1ጢሞ 4፡1-8

**መግቢያ፡-** ባለፈው ጥናታችን የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋዮች (ተከታዮች) በነገር ሁሉ ታማኞችና ያለነቀፋ መኖርን በመለማመድ በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት ዉስጥ እንዴት መመላለስ እንደሚገባን ተመልክተን ነበር፤ በዛሬው ጥናታችንደግሞ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠዉን መመሪያ እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በ ቁ 1 ላይ ባለዉ ሀሳብ መሰረት መንፈስ ቅዱስ በኋለኛው ዘመን ምን እንደሚሆን ነዉ የተናገረዉ?
2. ቁ 2-5 የሀሰት ትምህርት አስተማሪዎች ባህሪያት ምን ይመስላል? በወቅቱስ ያስተምሩት የነበረዉ ትምህርትምንድን ነበር? ከዕብ 13:4 እና ቁ 9 ላይ ካለዉ ሀሳብ ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
3. ቁ 6-7 መልካም የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?
4. በቁ 8 ሰዉነትን እግዚአብሔርን እንዲመስል ማስለመድ ጠቀሜታዉ ምንድን ነው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

5. እራስን እግዚአብሔርን ለመምሰል እንዴት ማስለመድ ይቻላል? ከህይወት ተሞክሮዎ በመነሳት ለህብረቱ ያካፍሉ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

በየዘመናቱ ቤተ ክርስቲያንን ከሚገዳደሯት ነገሮች አንዱና ዋንኛው የሀሰት ትምህርት ነው። የሀስት ትምህርት ደግሞ ዋንኛ ምንጩ አጋንንት ነው። ይህንን ተግዳሮት የምንመክተዉ በእዉነት ቃል ላይ በተመሰረተ እዉቀትና እምነት ላይ እራሳችንን በማነፅ ፀንተን በመቆም ነው።

**የቃል ጥቅስ**

“… እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ።” 1ጢሞ 4:7

## **ጥናት 8**

## ለጢሞቴዎስ የተሰጠ መመሪያ

## (ክፍል ሁለት)

## የምንባብ ክፍል፥1ጢሞ 4፡9-16

**መግቢያ፦** ባለፈው ጥናታችን ሀሰተኛ አስተምሮን በመመከት እራሳችንን በሚገባ በእዉነተኛ ቃል ላይ በተመሰረተ እውቀትና እምነት ላይ እራሳችንን ማነፅ እንዴት እንደሚገባን ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐዋርያዉ ጳውሎስ በዚሁ ሀሳብ ላይ ጨምሮ ጢሞቴዎስን የመከረውን ቀጣይ ምክር እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ቁ 9 "ይህ ቃል የታመነ ሁሉም እንዲቀበሉት የተገባ ነው" የተባለዉ የትኛዉ ቃል ነዉ? ለምን?
2. በቁ 11-12 መሰረት ሐዋርያዉ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የመከረዉ ክርስቲያናዊ የኑሮ ዜይቤ ምን እንደሚመስል ተወያዩበት።
3. በቁ 13-14 ላይ ሐዋርያዉ ጳውሎስ ተመልሶ ወደ ጢሞቴዎስ እስኪመጣ ድረስ ጢሞቴዎስ እንዲጠነቀቅ ወይምትኩረት እንዲሰጥ የታዘዘው ምንድን ነው? ተወያዩበት።
4. ቁ 15-16 "ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ" ብሎ ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እንዲያደርጋቸው የመከረው ምክር ምንድንነው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

5.ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ እድገትን እንዴት እንደሚለማመዱ የግሎትን ልምድ ያካፍሉ ።

❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

አንድ ልጅ በአካል ከተወለደ በኋላ በደረሰበት እድሜ ሁሉ የሰዉነት እድገቱ ከእድሜዉ ጋር ተመጣጣኝ መሆኑ የጤናማ እድገት መለኪያው የሆነዉን ያህል አንድ ክርስቲያን ደግሞ በመንፈሳዊ ህይወቱ እንዲሁ ጤናማ እድገት እንዳለው በነገር ሁሉ ማደጉን ሊያሳይ የገባል።

**የቃል ጥቅስ**

"ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ፥ ይህንም አዘውትር።" 1ጢሞ 4፡15

## <u>ጥናት 9</u>

## ስለ መበለቶች፤ ሽማግሌዎችና ባሪያዎች የተሰጠ መመሪያ

## (ክፍል አንድ)

## <u>የምንባብ ክፍል፡ 1ጢሞ 5፡1-16</u>

**<u>መግቢያ፦</u>** አማኞች በእዉነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ላይ በተመሰረተ እውቀትና እምነት ላይ በመታነፅ  በመንፈሳዊ ህይወታቸዉ በነገር ሁሉ ማደጋቸውን ሊያሳዩ እንደሚገባ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በተለያየ የዕድሜ ክልል ያሉትን አማኞች በምን ዓይነት መንገድ መመልከት እና ማገልገል እንደሚገባ እንወያያለን።

**<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>**

1. በንባብ ክፍሉ ውስጥ ሐዋርያዉ የዘረዘራቸው የዕድሜ ክልል በመዘርዘር እነኚህን አማኞች ጢሞቴዎስ በምንአይነት አኳኋን እንዲመለከታቸዉ እና እንዲያገለግላቸው ነው መመሪያ የተቀበለው? ተወያዩበት።

2. በቁ 3 ላይ ሐዋርያዉ በእውነት ባልቴቶች የሆኑትን ይላል፤ በእውነት ባልቴቶች የሆኑት በምን ዓይነት ሥነምግባርሊኖሩ እንደሚገባ የተናገረዉን ሃሳብ በማብራራት በተጨማሪ በዘሬዉ ጥናታችን ዉስጥ እንደእዉነተኛ ባልቴት ያልተቆጠሩት ሴቶች ደግሞ ከምን የተነሳ እንደሆነ ተወያዩበት።
3. ለእዉነተኛ ባልቴት መመዘኛ የቀረቡትን ሃሳቦች በመግለፅ፤ በምን ዓይነት መንገድ ቤተ ክርስቲያን ልታገለግላቸዉእንደሚገባ ክፍሉን ከ ያዕ 1፡27 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
4. በቁ 8 ላይ አማኞች ለቤተሰቦቻቸው ያለባቸው ሀላፊነት ምንድን ነው? ሃላፊነታቸውንስ የማይወጡትስ እንዴትእንደተገለፁ ተወያዩበት።

**<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>**

5. ቤተ ክርስትያን የክርስቶስ ናት፤ በክርስቶስ አምነው የዳኑ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያቀፈች እና ሁሉንምበዕኩል በፍቅር ማገልገል አለባት። የእድሜ ባለጠጎችን ከማገልገል ጋር ያጋጠሞዎት ገጠመኝ ወይም ተሞክሮ ካለዎት ለህብረቱ ያካፍሉ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት**

**<u>ማጠቃለያ</u>**

ዘጸ 20፡12 አባትህንና እናትህን አክብር። ምንም እንኳን ሰዎች ክርስትናን በዓለም ላይ ካሉት ሐይማኖቶች እንደአንዱ ቢቆጥሩትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ላይ ያለዉ የሃይማኖቶች ቁጥር ስላነስ አንድ ሃይማኖት ሊጨምር አልመጣም። ክርስትና ህይወት ነዉ። በእዉነተኛዉ የእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ ዘላለማዊነት ያለዉ ልንኖርዉየሚገባ ህይወት ልንኖርበት የሚገባ መንገድ እንዲሁም አጥብቀን ልንይዘዉ የሚገባ እዉነት ነው። በዛሬው ጥናታችን እንደተነጋገርነዉ እና እንዳየነዉ ትምህርት ሰዉንም እግዚአብሔርም ልንጠቅምና ልናገለግል ይጠበቅብናል።

**<u>የቃል ጥቅስ</u>**

“ሽማግሌ የሆነውን አትገሥጸው፥ እርሱን ግን እንደ አባት፥ ጎበዞችን እንደ ወንድሞች፥ የሸመገሉትን ሴቶች እንደ እናቶች፥ቆነጃጅቱን እንደ እኅቶች በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው።” 1ጢሞ 5፡1-2

## **ጥናት 10**

## **ስለ መበለቶች፤ ሽማግሌዎችና ባሪያዎች የተሰጠ መመሪያ**

## **(ክፍል ሁለት)**

## **የምንባብ ክፍል፡ 1ጢሞ 5፡17-25**

**መግቢያ፦** ባለፈው ጥናታችን በተለያየ የዕድሜ ክልል እና ፆታ ያሉትን አማኞች በምን ዓይነት አኳኋን ማየት እና ማገልገል እንደሚገባን ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደገሞ በመካከላችን ሆነዉ በመስበክ፤ በማስተማር፤ በፀሎት እና በተለያዩ አገልገሎት የሚደክሙትን እንዴት መደገፍ እንዳለብን እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በ ቁ 17 ላይ የተዘረዘሩት ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ ይጥቀሱ። የተዘረዘሩበትስ ምክንያት ምንድን ነዉብለዉ ያስባሉ?
2. ከቁ 17-18 ላይ ያለዉን ሀሳብ ከዘዳ 18፡1-8 ላይ ካለዉ ሀሳብ ጋር በማዛመድ እግዚአብሔር በቤቱ ዉስጥ ስለሚያገለግሉት አገልጋዮች ምን ያህል ግድ እንደሚለዉ ተወያዩበት።
3. ፍርድን እና ፍትህን በተመለከተ ከቁ19-22 ባለዉ ለጢሞቴዎስ ጳውሎስ የመከረዉን ምክር በእያንዳንዱ ሃሳብላይ ተወያዩበት።
4. በቁ 24 ላይ ባለዉ ሀሳብ መሰረት "የአንዳንዶች ሰዎች ኃጢአት የተገለጠ ነው ፍርድንም ያመለክታል፥ ሌሎችን ግንይከተላቸዋል" ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነዉ? ስለተገለጠ፤ ስለተሰወረ ኃጢአት እንዲሁም ስለ መልካም ስራ የተናገረዉን ተወያዩበት?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

5. እግዚአብሔርን ማገልገል ትልቅ መታደል ነው። ከእውነተኛ አገልጋዮች ጋር መቆምና አገልግሎታቸዉን መደገፍም እንደዝሁ ትልቅ መታደል ነው። እርሰስ ከእዉነተኛ አገልጋዮች ጋር መቆም እንደሚያስፈልግ ተረድተዋል? በዚህ ረገድ ምስክርነት ካሎት ለቡድኑ ይመስክሩ።

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫዬንም ጨርሻለሁ ብሎ ሐዋርያዉ ጳውሎስ ለመናገር የደፈረዉ በብዙ ተጋድሎ መከራብዙ ድብደባ እና ስቃይ በፀሎት በከፍተኛ ሁኔታ ያለመታከት ጌታን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከመጨረሻው ከአገልግሎትበኃላ ነው። እንዲህ ባለ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ወገኖች ከሁላችንም ከፍተኛ የሆነ ክብር ድጋፍ እና ፀሎትናበሚያስፈልጋቸውም ነገር ሁሉ አብሮ መቆም ይኖርብናል። የዘላለም በሆነ ሕይወት በሚገኝበት እንጅ በጊዚአዊ እና በምድራዊ ነገር ብቻ ስላላገለገሉን በመሃከላችን ስላሉት አገልጋዮች የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን።

**የቃል ጥቅስ**

"እንዲሁ መልካም *ሥራ* ደግሞ የተገለጠ ነው፥ ያልተገለጠም ከሆነ ሊሰወር አይችልም።" 1ጢሞ 5:25

<u>**ጥናት 11**</u>

<u>**የገንዘብ ፍቅር**</u>

<u>**የምንባብ ክፍል፡ 1ጢሞ 6፡1-10**</u>

<u>**መግቢያ፡-**</u> ባለፈው ጥናታችን ሐዋርያዉ ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪነቱ በቤተ ክርስቲያን ዉስጥ ያሉትን ምዕመናን ይልቁንም ደግሞ መበለቶችንና ሽማግሌዎችን እንዴት መያዝ እንዳለበት የመከረውን ምክር ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ክርስቲያኖች በገንዘብ ፍቅር ዉስጥ እንዳይወድቁ ሊያደረጉት ስለሚገባው ጥንቃቄ የተፃፈዉን የጳውሎስን መልዕክት በዝርዝር እንመለከታለን።

<u>**የመወያያ ጥያቄዎች**</u>

1. በ ቁ 1 እና 2 ላይ ጳውሎስ ባሮች ጌቶቻቸዉን ይልቁንም በጌታ የሆኑትን በምን አይነት መልኩ እንዲያገለግሏቸውነው የሚያዘው?
2. በቁ 4-5 ባለዉ ክፍል ዉስጥ የተጠቀሱ ሰዎች "እግዚአብሔርን መምሰል" ትርፋማ እንደሆነ ማሰባቸዉ ስህተቱምን ላይ ነዉ? ለምን?
3. በቁ 6 ላይ ላሉት ሰዎች እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፍያ የሚሆንላቸዉ እንዴት ነው? ከቁ 4-5 ካሉት ሰዎችጋር ያስተያዩት።
4. ቁ 9-10 ዉስጥ ያለዉን ሀሳብ በቁ 5 ላይ ካለዉ ሀሳብ ጋር በማዛመድ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ለምንእንደሆነ ተወያዩበት።
5. ቁ 10 መሰረት ሰዎች ካላቸው የገንዘብ ፍቅር የተነሳ ራሳቸውን በብዙ ሥቃይ ሊወጉ የሚችሉት እንዴት ነው? ከማቴ 6:24 ጋር ያዛምዱ።

<u>**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**</u>

6. ገንዘብ በህይወትዎ ሊይዘዉ የሚገባዉን ቦታ ትቶ ከእግዚአብሔር መንገድ እንዳያወጣዎ እራሰን እንዴት ነዉየሚጠብቁት?

- **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

<u>**ማጠቃለያ**</u>

ምንም እንኳን በእለት ኑሮአችን የገንዘብ አስፈላጊነት የጎላ ቢሆንም ከእለት ኑሮአችን አልፎ በዚህ ዓለም ላይ ላለው ትርፍ ነገር ስንል ገንዘብ ለማግኘት የምናደርገው ሩጫ ከእግዚአብሔር መንገድ እንዳያወጣን በመጠን መኖርን ማወቅና ባለን ነገር መደሰት መቻል ይገባናል።

<u>**የቃል ጥቅስ**</u>

"ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።" 1ጢሞ 6:10

**ጥናት 12**

**ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው አደራ**

**የምንባብ ክፍል፡ 1ጢሞ 6፡11-21**

**መግቢያ፡-** ባለፈው ጥናታችን የእግዚአብሔር ሰዎች በመጠን የሆነ ኑሮ እየኖሩ እራሳቸውን ከገንዘብ ፍቅር እንዴት ሊጠብቁ እንደሚገባ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጢሞቴዎስ የተቀበለው የወንጌል አደራ እንዴት በታማኝነት ሊጠበቅ እንደሚገባ እና ጥሪዉን የሚመጥን ህይወት እንዲኖር የሰጠውን ማሳሰቢያን እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁ 11- 12 ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቲዎስ እንዲሸሸውና ደግሞም አጥብቆ እንዲከተለው የሚያዘው ነገርምንድን ነው?
2. በቁ 12 "መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል" ብሎ ጳውሎስ ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
3. በቁ 14 ጢሞቲዎስ ያለእድፈትና ያለነቀፌታ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንዲጠብቅ ሲያዝው የትዕዛዙ ክብደት ምንያህል ይመስሎታል? ከቁ 13-16 ያለውን ሙሉ ሀሳብ በማየት ተወያዩበት።
4. በቁ 17- 19 ባለው ሀሳብ መሰረት የባለጠጎች ተግዳሮት ምንድን ነው? ይህንን ተግዳሮትስ እንዴት ነው መወጣት የሚገባቸው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

5. በገንዘብ ባለጠግነት እና በመልካም ስራ ባለጠግነትን ፤ ከእግዚአብሔር ቃል አንፃር እንዴት ይረዱታል?

❖ **በዛሬው ምንባብ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ሀሳብ ካለ ተወያዩበት።**

**ማጠቃለያ**

እግዚአብሔር የበረከት አምላክ እንደመሆኑ መጠን ልጆቹን በሀብት ይባርካል። ይህ ሀብት ወደ እኛ ሲመጣ አይኖቻችንን ከሰጭው ላይ በማንሳት ወደስጦታው ላይ እንዳናደርግ ይልቁንም የተሰጠንን ሀብት መልሰን ለመንግስቱ ስራ በማዋል እግዚአብሔርን በዛ ልናከብርበት ይገባል።

**የቃል ጥቅስ**

"አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል." 1ጢሞ 6:11

# <u>ክፍል ሦስት</u>

## የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት

## ለጢሞቴዎስ

# <u>ሁለተኛ</u>

## መግቢያ

### ጸሃፊውና የተጻፈበት ዘመን

የጢሞቴዎስ መልዕክትን የጻፈው ሃዋሪያው ጳውሎስ እንደሆነ በመልዕክቱ የመጀመሪያው ክፍል (1፡1) ላይ በግልጽ ተቀምጧል። ከዚህም በተጨማሪ በመልዕክቱ ውስጥ በርካታ ቦታዎች ላይ የመልዕክቱ ጸሃፊ ሃዋሪያው ጳውሎስ ስለመሆኑ ገላጭ ማስረጃዎች ተካትተው እናገኛለን። ይህንን መልዕክት ሃዋሪያው ጳውሎስ ከኣራተኛው የወንጌል ጉዞ በኋላ በ 66 እስከ67 ዓ.ም ገደማ በሮም በእስር ላይ እያለ እንደጻፈው ይገመታል።

### ታሪካዊ ዳራ

ሓዋሪያው ጳውሎስ ይህንን መልዕክት በሚያዘጋጅበት ዘመን የሮም ንጉስ የነበረው ኔሮ በቤተክርስቲያን ላይ ባስነሳው ጫናና ስደት የተነሳ ጳውሎስ በድጋሜ በወህኒ የመጣል ፈንታ አጋጥሞት ነበር። በተጨማሪም ከሉቃስ በስተቀር አጋሮቹ ሁሉ ከእርሱጋር አልነበሩም። እንዲያውም ዴማስም(4:10) ትቶት ሄደ ነበር። ከዚህም የተነሳ ይመስላል ጢሞቴዎስን በቶሎ ወደ እርሱ እንዲመጣ በመልዕክቱ ሁሉ ላይ (1:4፣ 4፡9) ሲያስገነዝበው እንመለከታለን።

### መልዕክቱ የተጻፈበት ዓላማ

ሓዋሪያው ጳውሎስ በጊዜው ከነበረው መከራና ስደት የተነሳ ስለወንጌል አገልግሎት ይጨነቅ ነበር። የህይወቱም ማብቂያ እንደደረሰ ባወቀ ጊዜ (4፡6) ልጅ አባቱን እንደሚያገለግል (ፊሊ 2፡22) አብሮት በትጋት ያገለግል ለነበረውና ስለ እግዚአብሄርስራ ከልብ ለሚገደው ለጢሞቴዎስ (ፊል 2፡22) ይህንን መልዕክት ሲጽፍ እናያለን። በመልዕክቱ ውስጥ በርከት ያሉ ሃሳቦችን ያነሳ ቢሆንም በጥቅል ስናየው ግን ጢሞቴዎስ አብሮት ሲያገለግል በጌታ ጸጋ ከእርሱ የተማረውንና በተግባር ያየውን ለሌሎች የማስተላለፍ ብቃት እንዳለው በሚገባ እንደተረዳ እናያለን።

ሓዋርያው ጳውሎስ ሸክም የሆነበትን የወንጌል ስራ እንዳይቃረን ለእርሱ አደራ በመስጠት እንደወሰነና ከዚህም የተነሳ ከግብዝነት የጸዳውን እምነቱን እንዲጠብቅ ከእርሱ የሰማውን ጤናማ የእውነት ቃል እንዲያስተምር ይመክረዋል። በእግዚአብሄርም ፊት ከአጉል ክርክርና የጎልማሳነት ምኞት በመራቅ በጽድቅ እየተመላለሰ ትርጉም ያለው ኑሮ ተገቢ መሆኑንያስገነዝበዋል። በአገልግሎቱም መከራን ሳይፈራ ራሱን እየገዛ በትዕግስትና በጥበብ የደከሙትን እንዲያቀና እያሳሰበው ጌታን በእርሱ የጀመረውን በጎ ስራ የሚፈጽም አምላክና አባት መሆኑን ያረጋግጥለታል።

በተጨማሪም ራሱን ለጌታ የሚጠቅም የክብር እቃ አድርጎ እንዲቆጥርና ለወንጌል አገልግሎት የክብር ብድራት እንደሚያስገኝይገልጽለታል። ሓዋሪያው ጳውሎስ በመልዕክቱ ከገለጸው በላይ ጢሞቴዎስ ወደ ሮም መጥቶ ሊያወያየው እንደሚወድ እንመለከታለን።

**<u>መልዕክቱ የያዛቸው ክፍሎች</u>**

ይህ መልዕክት ለመጀመሪያ ተደራሹ ለጢሞቴዎስ የተጻፈ ቢሆንም ዘመንን አሻግሮ የሚያውቅ የእግዚአብሄር መንፈስ በዚህዘመን ላለን ለእኛ የሚሆን መልዕክት በውስጡ አስቀምጧል። ይህንን መልዕክት ለማጥናት መወሰናችን ለህይወታችን ጊዜከማይሽረው የህይወት ቃልን ተካፋዮች እንድንሆን ያደርገናል። በመሆኑም መልዕክቱን ለማጥናት እንዲረዳ ከዚህ በታችእንደተዘረዘረው በእርስ ተከፋፍሎ ተቀምጧል።

| | | |
|---|---|---|
| **ምዕራፍ 1** | | |
| | 1 እስከ 4 | የጳውሎስ መግቢያ |
| | 5 እስከ 14 | ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ስለመጨነቁ |
| | 15 እስከ 18 | ጳውሎስ የነበረበት ሁኔታ |
| **ምዕራፍ 2** | **ለጢሞቴዎስ የተእጠ ልዩ መመሪያ** | |
| | 1 እስከ 13 | ለትዕግስት የቀረበ ጥሪ |
| | 14 እስከ 26 | ከአጉል ክርክር እንዲርቅ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ |
| **ምዕራፍ 3** | **ስለ መጨረሻው ዘመን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ** | |
| | 1 እስከ 9 | የሚያስጨንቅ ዘመን |
| | 10 እስከ 17 | ዘመናትን የመዋጊያ ዘዴዎች |
| **ምዕራፍ 4** | **የጳውሎስ የስንብት ንግግር** | |
| | 1 እስከ 5 | ቃሉን እንዲሰብክ የተሰጠው ትዕዛዝ |
| | 6 እስከ 8 | የጳውሎስ የድል ተስፋ |
| | 9 እስከ 22 | የመጨረሻው ሰላምታ |

## ጥናት 1

## ስለታማኝነት ማበረታቻ

## የምንባቡ ክፍል:- 2ኛ ጢሞቴዎስ 1: 1-7

**መግቢያ**:- በዛሬው ጥናት በሃዋሪያው ጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት አብሮት ለሚደክመው ለጢሞቴዎስ ስለወንጌል አገልግሎት ታማኝ እንዲሆንና ከግብዝነት የተጠበቀ እምነቱን እንዲጠብቅ ሲያበረታታው እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ቁጥር 1 ን በመመልከት "በክርስቶስ ኢየሱስ ቃል በተገባው የህይወት ተስፋ መሰረት" ሲል እግዚአብሄር አብ በልጁበኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰጠውን ተስፋና መሰረቱን አስረዳ።
2. ቁጥር 3 ን በመመልከት "በወንጌል ሳላቋርጥ ሌሊትና ቀን በጸሎት ስለአንተ እተጋለሁ" ሲል ለወንጌል አገልግሎትና በወንጌል አገልግሎት ውስጥ በትጋት ለሚያገለግሉ አገልጋዮች መጸለይ ምን ያህል አስፈላጊ ስለመሆኑ ተነጋገሩበት?
3. ቁጥር 4 እስከ 5 በመመልከት ሃዋሪያው ጳውሎስ በጢሞቴዎስና በቤተሰቦቹ ያየውን ከግብዝነት የጸዳ እምነት ምንሊመስል እንደሚችል በማሰብ ተወያዩበት በተጨማሪም በዚህ ዘመን ከግብዝነት የጸዳ እምነት ምን ሊሆን እንደሚገባው ተግባራዊ ምሳሌዎችን በማንሳት ተወያዩበት።
4. ቁጥር 6 በመመልከት የእግዚአብሄር ስጦታ ከሰጪው ከእግዚአብሄር የሆነና እርሱን ብቻ የሚያከብር መሆኑን ማወቃችን አይኖቻችንን ከስጋ ለባሽ ላይ እንድናነሳ እንዴት ሊጠቅመን እንደሚችል ክፍሉን በጥሞና በማንበብተወያዩበት?
5. ቁጥር 7 ን በመመልከት እግዚአብሄር ለልጆቹ የሰጠው መንፈስ ምን ዓይነት ባህርይ እንደሚያላብስና ለምድራዊውም ሆነ ለመንፈሳዊ ህይወታችን ዕድገት እንዴት እንደሚረዳን ከተግባራዊ ተሞክሮ ጋር በማያያዝ አስረዳ?

## ከሕይወት ጋር ማዛመድ

6. ጸሎት በህይወትህ ውስጥ ምን አይነት ቦታ ሊይዝ ይገባዋል ትላለህ? ምንስ ያህል የምስጋና ጸሎት በህይወትህ ተለማምደሃል?
7. በዛሬው የምንባብ ክፍል ውስጥ በመወያያ ጥያቄዎች ያልታቀፉ ሃሳቦች ካሉ በማንሳት ተወያዩበት።

**ማጠቃለያ**

ክርስትና የእግዚአብሄር አብ ፍቅር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ስራ እንዴት እንደተፈጸመና ይህንንም መንፈስ ቅዱስእንዴት እንዳጸናው የምናውጅበት ህይወት እንጂ ስጋና ደም ይህንን ክብር የሚጋራበት አይደለም። አማኞች ካለግብዝነት ሳንፈራ ራሳችንን የመግዛት መንፈስ ለሰጠን ለእግዚአብሄር አምላካችን ክብርን ሁሉ እየሰጠን ከእኔነትና ከታይታ ለጸዳ ህይወትና አገልግሎት እንደተጠራን ልንገነዘብ ይገባናል።

**የቃል ጥቅስ**

"እግዚአብሄር የሃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ ሰጠን እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንም" 2ኛ ጢሞ 1፡ 7

## ጥናት 2

## ስለታማኝነት ማበረታቻ

## የምንባብ ክፍል: 2ኛጢሞ 1:8-18

**መግቢያ፡**ባለፈው ጥናት ካየነው በመቀጠል በዛሬውም ጥናት በሃዋሪያው ጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት አብሮት ለሚደክመው ለጢሞቴዎስ ስለወንጌል አገልግሎት ታማኝ እንዲሆንና ከግብዝነት የተጠበቀ እምነቱን እንዲጠበቅ ሲያበረታታው እንመለከታለን ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ቁጥር 8 በመመልከት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በተጠራንበት ወንጌል ሳናፍር በጥበብና በማስተዋል እንዴትልንመላለስ እንደምንችል ተወያዩበት።
2. ቁጥር 8 እስከ 12 በመመልከት ስለክርስቶስ ወንጌል በእግዚአብሄር ሃይል መከራን ለመቀበል አቅም የሚኖረውእንዴት ነው? “መከራ” ስንል እንደቀደሙት አማኞች ስደትና እስራት ብቻ ሳይሆን ቃሉን ለመታዘዝ በየዕለት ህይወታችን ዋጋ መክፈልን እንደሚያካትት መረዳታችን ምን ያህል እንደሚጠቅመን አስረዳ?
3. ቁጥር 9 እስከ 11 በመመልከት እግዚአብሄር ልጆቼ ብሎ ወደመንግስቱ ሲጠራን ከዘላለም ዘመናት በፊት በልጁ በኩልሊሰጥ የወሰነውን የጸጋ ስጦታ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ በኩል እንዴት እንደፈጸመው እስረዳ?
4. ቁጥር 12 ን በመመልከት “ከእኔ የሰማኸውን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነትና ፍቅር የጤናማ ትምህርት ምሳሌ አድርገህ ያዝ” ሲል ምን ማለቱ ነው? እንዴት ጤናማ ካልሆኑ ትምህርቶችና መንፈሳዊ የሚመስሉ ልምምዶች ልንጠበቅ እንደምንችል ተግባራዊ ምሳሌዎችን በማንሳት ተወያዩበት።

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. ቁጥር 15 እስከ 17 በመመልከት አማኞች በጌታ ላይ ያላቸው እምነት ሲዝልና ከነበሩበት ፈቀቅ ሲሉ ስታይ ምንማድረግ አለብኝ ብለህ ታስባለህ?
7. በወንጌል አገልግሎት ከሚደክሙት ጋር ባለን አቅም ሁሉ መተባበርና የጸጋችንን ድርሻ በመንፈስ ቅዱስ በመደገፍመወጣት እንደሚገባን ያለህን መረዳትና ተሞክሮ በማንሳት ተወያዩበት።

**ማጠቃለያ**

እግዚአብሄር አብ አስቀድሞ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሁሉን ሊጠቀልል በወሰነው መሠረት የሰጠን ጸጋ በሞቱና በትንሳኤው ተገልጦ አይተናል። ይህም የምስራቹን ወንጌል ሳንፈራ በድፍረት እንደሚገባ እንድንመሰክር ጉልበት ይሆነናል።ጌታችን በፈተና ሁሉ ሊረዳን በእኛም የጀመረውን እስከመጨረሻው ሊጠብቅ የታመነ ስለሆነ የወንጌልን አደራ ለመጠበቅ ልንተጋ ይገባል።

**የቃል ጥቅስ**

‘ያመንኩትን እርሱን ስለማውቅ አላፍርበትም፣ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያች ቀን ድረስ መጠበቅ እንደሚችል ተረድቼያለሁ።” 2ኛ ጢሞ 1 1 12

<u>**ጥናት 3**</u>

**ስለ ትዕግስት የቀረበ ጥሪ**

<u>**የጥናት ክፍል 2ኛ ጢሞ 2: 1 - 13**</u>

<u>**መግቢያ፡**</u> ባለፈው ጥናታችን ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለአገልግሎት እንዲነሳሳ ሲያበረታታውና በእስያ አብረውት የነበሩትን ሰዎች ሁሉም እንደተዉት ሲናገር ተመልክተን ነበር። በዛሬ ጥናታችን ይሄው ብቸኝነትና ስደት በጢሞቲዎስም ላይ ሊደርስ እንደሚችልና እርሱ ግን ዋጋውን ተመልክቶ (ተምኖ) ጌታን በድፍረት እንዲከተለው ሲመክረው እናያለን።

<u>**የመወያያ ጥያቄዎች**</u>

1. በቁ. 1 "አንተ ግን "ሲል ካለፈው ምዕራፍ መጨረሻ ጋር ምን ቀጣይነት ወይንም ተዛማጅነት እንዳለው ያመለክታል?
2. በጸጋ መበርታት ማለት ምን ማለት ነው?
3. ከቁጥር 1 - 2 ባለፈው ክፍል ጢሞቴዎስ እንዲያደርግ የመከረው ትዕዛዝ ምንድነው? ትዕዛዝን ተቀብሎ የማድረግአስፈላጊነት አስረዳ።
4. በጥሩ ወታደር፣ በሚደክም ገበሬና፣ በአትሌት መካከል ያለውን ተመሳሰይነት ምንድነው?
5. በቁጥር 7 የማስተዋል አስፈላጊነቱ ምንድነው? ማስተዋል እንዴት ሊመጣ ይችላል?
6. በቁጥር 8 ከዳዊት ዘር የሆነውን ኢየሱስን አስብ ሲል ይመክረዋል። ከዳዊት ዘር መሆኑን ማወቁ ለምን አስፈለገ?የማሰቡስ ጥቅም ምንድነው?
7. በቁጥር 10 መከራን ታግሶ እንዲጸና ያደረገው ምንድነው? ከመለወጡ በፊት ካለው ህይወቱ ጋር አስተያይተህአስረዳ።
8. ከክርስቶስ ጋር መሞት፣ መኖርና፣ መክበር ምንድነው?

<u>**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**</u>

9. ወንጌልን የማዳረስና የትውልድ ሃላፊነት እንዳለብህ አውቀህ ምን ያህል ለሌሎች አደራውን በማስተላለፍ ላይትገኛለህ?
10. ከክርስቶስ ጋር ለመኖርና ለእርሱ ክብር በሚያመጣ ኑሮ ብቻ ለመጠመድ እንደተጠራን ምን ያህል ገብቶሃል?
11. የእግዚአብሄርን ታማኝነት ለአንተ/ለአንቺ በዘመንህ የሆነውን አስረዳ።

<u>**ማጠቃለያ**</u>

ለክርስቶስ ለመኖርና እርሱን ለማገልገል የተጠራን ሲሆን እኛ ደግሞ ለዚህ ጥሪ ራሳችንን ሳንቆጥብ በሙሉ እንድንሰጥተጠርተናል። እግዚአብሄር በክርስቶስ ለእኛ ያደረገውን ብናስብ ለዘመናችን ብርታት ይሆንልናል።

<u>**የቃል ጥቅስ**</u>

እርሱ ሁልጊዜ የታመነ ነው። 2ኛ ጢሞ 2: 13

## ጥናት 4

## እግዚአብሔር የሚቀበለው አገልጋይ

## የጥናት ክፍል 2ኛ ጢሞ 2: 14 - 26

መግቢያ፡ ባለፈው ጥናታችን ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በፈተና ሳይፈታ(ሳይንበረከክ) ዋጋውን ተመልክቶ ጌታን እንዲያገለግለው ሲመክረው ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ምሳሌነት ባለው አኗኗሩ ለትምህርቱ ሊያደርገው ስለሚገባው ጥንቃቄሲያሳስበው እናያለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁጥር 14 ላይ በቃል መጣላት ምንድነው? የእግዚአብሔር ቃል በሰው ህይወት ሊያመጣ (ሊያደርግ) የሚገባው ለውጥ ከዚህ በምን ይለያል?
2. ከቁጥር 14 - 16 በተገለጸው መሰረት ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚያሳፍር ሰራተኛ እንዳይሆን ምን እንዲያደርግ ይነግረዋል/ይመክረዋል? ጳውሎስን የሚያሳፍርን ሰራተኛ በምን ይገልጸዋል?
3. ከቁጥር 16 – 18 ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዲያስወግድ የሚመክረው ነገር ምንድነው? ስለኢየሱስ ትንሳኤ ያላቸው መረዳት የተሳሳተ መሆኑ ምን ጉዳት ያመጣበታል?
4. በቁጥር 19 ጌታ የራሱ የሆኑትን እንደሚያውቅ ሲናገር በክፍሉ የተጠራው ህዝብ ለምን እንደተጠራ ያሳስበዋል (ያስገነዝበዋል)?
5. ከቁጥር 20 – 21 አማኝ (አገልጋይ) ለክብር የሚሆን የተቀደሰ ዕቃ አድርጎ ራሱን የሚያቀርበው በምን መንገድ ነው?
6. በቁጥር 22 ክፉ የጎልማሳነት ምኞት ምንድነው? ጢሞቴዎስን እንዲያደርግ የተመከረው ምንድነው? ለምን?
7. ከቁጥር 23 – 24 የጌታ ባህርያቶቹ (መለያ) ምን እንዲሆን ያመለክታል?
8. ከቁጥር 25 – 26 ተቃዋሚዎች (ሃሰተኞች) ከተያዙበት ከሰይጣን ባርነት መውጣት እንዴት ይችላሉ? የሚመለሱትንሰዎች በምን መንገድ እንዲቀበል ይመክረዋል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

9. ጌታ የራሱ የሆኑትን ማወቁ ለየዕለት ኑሮህ ሊሰጥህ የሚገባውን ድፍረት አስረዳ።
10. የእግዚአብሄር ቃል የጠፉትን የመመለስ ጉልበት እንዳለው አውቀህ ቃሉን ሁልጊዜ እንዴት ልትናገር እንደሚገባህአካፍል።

**ማጠቃለያ**

ብዙዎች የእግዚአብሄርን ቃል በሚያጣምሙበት የመጨረሻው ዘመን ውስጥ ብንኖርም እኛ ግን የጌታ መሆናችንን አውቀንለእውነቱ ቃል ህይወታችንን ሰጥተን፣ ለሌሎች መመለስ ምክንያት ልንሆን እንደተጠራን ማወቅ ይገባል።

**የቃል ጥቅስ**

በንጹህ ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርንና ሰላምን ተከታተል። 2ኛ ጢሞ 2፡22

## ጥናት 5

# የመጨረሻው ዘመን ክህደት

## የጥናት ክፍል 2ኛ ጢሞ 3፡ 1 - 9

**መግቢያ፡-** ባለፈው ጥናታችን ጢሞቴዎስ ከተቃውሞው በበለጠ ጌታን በጽናት እንዲያገለግለው ሲያደፋፍረው የተመለከትን ሲሆን በዛሬው ጥናታችን ደግሞ የጊዜውን አስቸጋሪነት ሲያሳየውና በዚያ ውስጥ ግን እምነቱ በእግዚአብሄር የጸና እንዲሆን ሲያበረታታው እናያለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁጥር 1 ላይ "በመጨረሻው ዘመን" ሲል የትኛውን ጊዜ ያመለክታል?
2. በቁጥር 2-5 የተጻፉትን ባህርያትና መገለጫቸውን አብራርተህ አስረዳ።
3. ሰዎች በመጨረሻው ዘመን ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ ሲል ራስን በመውደድ ያለውን ክፋት(ጥፋት) ምንድነው?
4. ገንዘብን መውደድ ሃጢያት የሆነበት ምክንያቱ ምንድነው?
5. በቁጥር 5 በተገለጸው መሰረት ሰዎች የአምልኮ መልክ ኖሯቸው ሃይሉን መካድ የሚችሉት እንዴት ነው?
6. በቁጥር 5 መጨረሻ "ከእነዚህ ራቅ" ይላልና የመራቅ አስፈላጊነቱ ምንድነው? በባለፈው ጥናት 2ኛ ጢሞ 2፡ 24-25 ካለው ጋር እንዴት እናስታርቃለን?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

7. በቁጥር 6 - 7 እየተማሩ እውነትን ወደማወቅ አለመድረስ የሚመጣው ከምንድነው? ውጤቱስ?
8. በአሁኑ ጊዜ በቁጥር 6 - 8 በተገለጸው መሰረት እነዚህ ሰዎች የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተክርስቲያንንየሚጎዱበት መንገድ አስረዳ።
9. በቁጥር 9 መሰረት በእግዚአብሄር እውነት ላይ ያልቆመን ህይወት አደጋ አስረዳ።

**ማጠቃለያ**

የምንኖርበት ዘመን የመጨረሻው ዘመን እንደሆነ ተረድተን ብዙ አስተማሪዎችና ሰዎች እምነትን በአንደበታቸው በመናገር አካሄዳቸውን ግን ጌታን የማያሳይ ቢሆንም ሳንደናገት ለተጠራንበት ጌታና ህይወት ታማኞች እንድንሆን እግዚአብሄር ይርዳን።

**የቃል ጥቅስ**

የአምልኮ መልክ አላቸው፣ ሃይሉን ግን ክደዋል። 2 ጢሞ

## **ጥናት 6**

## **የጳውሎስ አደራ ለጢሞቴዎስ**

**የምንባቡ ክፍል 2ጢሞ 3:10 -17 ና 2ጢሞ4: ከ 4:1-5**

**መግቢያ :** ባለፈው ጥናት ሓዋሪያው ጳውሎስ በመጨረሻው ዘመን እንዴት አስጨናቂ ጊዜ እንደሚሆንና በዚያም ዘመን የሰዎች ባህርይ ምን እንደሚመስል አጥንተን ነበር። በተለይም ደግሞ የአምልኮት መልክ ያላቸው ነገር ግን ሃይሉን የካዱት እንዴት ራሳቸውንና እንደዚሁም በእምነታቸው ያላደጉትና ያልዳኑትን እንዴት ወደ አደጋ እንደሚያስገቡ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሓዋሪያው ጳውሎስ የራሱ የህይወት ጉዞና እንደዚሁም በመታገስና በመጽናት ያሳለፋቸውን ምሳሌ በመጠቀም ጢሞቴዎስን ሲያበረታታና የጀመረውን አገልግሎት ጠንክሮ እንዲፈጽም ሲያነሳሳው እናያለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**:

1. በቁጥር 10 እና 11 ላይ ሓዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለማበረታታት ሲል ያነሳቸውን ሃሳቦች ዘርዝር። ጳውሎስከዘረዘራቸው ምሳሌዎች ጢሞቴዎስ እንዲረዳው የፈለገው ምን ይመስልሃል?
2. ቁ 12 "በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሄርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።" ሲል ምን ማለቱነው?
3. ቁ 13 ክፉዎች በክፋት እየባሱ የሚሄዱት ለምንድነው ?
4. ከቁ14 እስከ 15 በተጠቀሰው መሰረት በእምነት ለመጽናት እንደዋና ምክር ሆነው የተሰጡት ምንድናቸው?
5. ከቁ16 እስከ 17 እንዴት ነው የእግዚአብሄር ሰው ለበጎ ስራና እግዚአብሄርን የሚያከብር ህይወት መኖር የሚችለው?
6. በምዕ 4:1 መሰረት ለምንድነው ሓዋሪያው ጢሞቴዎስን ለመምከር "የጌታ መገለጥና ፍርድ" የተጠቀመው?
7. ቁ. 2 ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ምንድነው የሚመክረው? በዝርዝር ተወያዩበት።
8. ከቁጥር 3 እስከ 4 "ሕይወት የሚገኝበት ትምህርት እንዴት ተብሎ ነው ሓዋሪያው ጳውሎስ የሚያስጠነቅቀው?
9. የጢሞቴዎስ የአገልግሎት ፍጻሜ እንዴት ባለ መልኩ እንዲሆን ነው ሃዋሪያው ጳውሎስ የሚመክረው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

**10.** በክርስቶስ እግዚአብሄርን እየመሰሉ ይሰደዳሉ? በእናንተ የህይወት ጉዞ ይህ እንዴት እንደሚመስል ተወያዩበት።

**ማጠቃለያ**

በዛሬ ጥናት እንዳየነው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ጸንቶ በእውነት መስበክና እግዚአብሄርን የሚያስከብር ህይወት መኖርእጅግ ትግል ያለበትና በትዕግስትና በእግዚአብሄር ቃል በመቆም የሚተላለፍ ህይወት እንደሆነ ተመልክተናል። በዚህ የህይወትመንገድ ስንጓዝ ቀድመውን በድልና በጽናት ያለፉትን እግዚአብሄር የተጠቀመባቸው ሰዎች እያየን ጉዟችንን በትዕግስትና በመጽናት እስከመጨረሻ መሮጥና መጓዝ እንዳለብን ተመልክተናል።

**የቃል ጥቅስ**

"በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሄርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።" 2ኛ ጢሞቴዎስ 3 12

## **<u>ጥናት 7</u>**
## **የሐዋርያው ጳውሎስ ሩጫ ፍጻሜ**
## **<u>የምንባብ ክፍል 2ኛ ጢሞ 4: 6-22</u>**

**<u>መግቢያ</u>**: ባለፈው ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በአገልግሎቱ እንዲጸናና እንደዚሁም ጠንክሮ እስከመጨረሻ በትዕግስት እንዲጓዝ የራሱን የህይወት ምሳሌነት በመጠቀም ሲያበረታታውና ሲመክረው አይተን ነበር። በዛሬ ጥናታችን ደግሞ ሓዋሪያውወደ ራሱ የህይወትና የአገልግሎት ፍጻሜው ምን እንደሚመስልና እንደዚሁም እስከመጨረሻ ድረስ የአገልግሎቱን ሓላፊነት ሲወጣና የመጨረሻውን ስንብት ሲያደርግ እንመለከታለን።

### **<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>**

1. ከቁጥር 6 እስከ 8 ባለው ክፍል መሰረት የሓዋሪያው የጳውሎስ የህይወቱና የአገልግሎቱ ፍጻሜ ምን ይመስልእንደነበር ተወያዩ።
2. በቁጥር 8 መሰረት ሓዋሪያው "የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል" ካለ በኋላ "ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉእንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።" ሲል ማለቱ ነው?
3. ከቁጥር 9 እስከ 12 ለምን ይሆን ሓዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወደ እርሱ በቶሎ እንዲመጣ በዝርዝር ስላለበትሁኔታ የገለጸለት?
4. ከቁ 12 -13 ሓዋሪያው ጳውሎስ በስም የጠቀሳቸው ሰዎች ስታዩ ስለ ሓዋሪያው ክፍሉ ምን የሚናገር ይመስልሃል?
5. ቁትር 14 መሰረት እንዴት ባለ መንገድ ነው የናስ አንጥረኛው እስክንድሮስ ለሓዋሪያው የከፋበት?
6. ቁጥር 14 እስከ 18 ሓዋሪያው ጳውሎስ የደረሰበት ተቃውሞና እንደዚሁም የጌታ ከእርሱ ጋር መሆን ስታዩስለወንጌል ስራ ክፍሉ የሚናገረው ምንድነው?
7. ከቁ 19 - 20 የሓዋሪያው ጳውሎስ የመልዕክቱ አፈጻጸም ስታይ ስለሓዋሪያው ማንነት የምትገነዘቡት ምንድነው?

### **<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>**

8. በትዕግስት ጸንቶና ጠንክሮ በጌታ የተገኘውን ህይወት በድል ለመፈጸም ዋና የምትላቸው ምክሮች ምንድናቸው?
9. የቀረ ሃሳብ ካለ ተወያዩበት።

### **<u>ማጠቃለያ</u>**

ሓዋሪያው ጳውሎስ በህይወቱና በአገልግሎቱ በስተመጨረሻ ያጋጠመውን ትግል እንደዚሁም የጌታ አብሮ መሆንና መጓዝ እኛም የጀመርነውን የክርስትና ህይወት ጠንክረን እስከጨረሻ እንድንጓዝ ያበረታታናል። ጌታ ሲገለጥ ደግሞ የጽድቅ አክሊልስለሚሰጠን በእምነትና በተስፋ እንድንጓዝ ያበረታታናል።


### **<u>የቃል ጥቅስ</u>**

"መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፣ ሩጫውን ጨርሼያለሁ፣ ሃይማኖትን ጠብቄያለሁ። ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል።" 2ኛ ጢሞ 4 7

# ክፍል አራት

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት

# ለቲቶ



**መግቢያ፦** የቲቶ መልእት ከ 1ኛ እና 2ኛ ጢሞቲዎስ ደብዳቤዎች ጋር በአንድነት Pastoral Epistle በመባል የሚታወቁ ሲሆን ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቱን ለቲቶ የጻፈው በቀርጤስ (Crete) በነበረው የሚስዮናዊ ጉዞው ያቋቋመውን ቤተክርስቲያን እንዲመራና በአካባቢው ባሉ አብያተክርስቲያናት ሽማግሌዎችን እንዲሾም ለመምከር ነው። ቀድም ሲል ቲቶ ከጳውሎስ ጋር በቀርጤስ ደሴት ለተወሰነ ጊዜ አብሮ እንዳገለገለ ይነገራል። በኋላም ጳውሎስ ቀርጤስን ለቆ በሄደ ጊዜ ቲቶ ቤተክርስቲያንን እንዲመራና አገልግሎቱንም አጥብቆ እንዲቀጥል በቀርጤስ ትቶት ሄደ (ቲቶ 1:5)።

**ጸሃፊው፦**

በመልዕቱ መግቢያ ላይ ጳውሎስ ማንነቱን "የእግዚአብሔር ባሪያ እና የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጳውሎስ" (ቲቶ 1:1) በማለት ደብዳቤው በእርሱ የተጻፈ መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ገልጿል።

**የመልዕክቱ ተደራሲ፦**

ጳውሎስ ደብዳቤውን "በሃይማኖት ኅብረት እውነተኛ ልጄ ለሚሆን ለቲቶ" (ቲቶ 1:4) በማለት ደብዳቤውን ለማን እንደጻፈ ገልጿል። ቲቶ የግሪክ አማኝ ሲሆን (ገላ 2:3) በጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት የክርስቶስን እውነት ወደ ማወቅየመጣ እንደሆነ ከቲቶ 1:4 መረዳት ይቻላል።

**መልዕክቱ የተጻፈበት ዘመን እና ቦታ**

የቲቶ መልእክት የተጻፈው ከ62-64 AD አካባቢ ነው። ይኸውም ጳውሎስ በመጀመሪያውና በሁለተኛው የሮም እስራቱ መከከል በመቄዶንያ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት እያገለገለ ባለበት ወቅት በቆሮንጦስ ወይም በኒቆጵልዮስ (ቲቶ 3:12) ሆኖየጻፈው ሳይሆን አይቀርም። በቲቶ 3:13 መሰረት መልዕክተኛ ሆነው ይህንን ደብዳቤ ለቲቶ ይዘው የሄዱት ምናልባት ዜማስን ወይም አጵሎስ ሳይሆኑ አይቀሩም።

**ታሪካዊ ዳራ፦**

ቄርጤስ (Crete) በሜድትራንያን ባህር ካሉት ትላልቅ ደሴቶች አንዷ ናት። ጳውሎስ ወደ ሮም ባደረገው ጉዞ ቄርጤስን ለአጭር ጊዜ ጎብኝቷል (ሐዋ. 27፡7-9፣ 12፣ 13)። ለአገልግሎት በተመለሰ ጊዜም ቲቶን አገልግሎቱን እንዲቀጥል በዚያ ትቶ ጢሞቴዎስን ደግሞ ወደ መቄዶንያ በሚሄድበት ጊዜ በኤፌሶን ትቶት ሄዷል (1ጢሞ 1፡3)። ምናልባትም የቲቶንም መልዕክት የጻፈው ከቲቶ ወይም ከቀርጤስ ለተላከ መልእክት ምላሽ ለመስጠት የላከው ሳይሆን አይቀርም።

የቄርጤስ ደሴት ሰዎች ታማኝነት በጎደለው፣ በውሸት፣ በጭካኔ እና በስግብግብነት ባህርያት የታወቁ ናቸው። ጳውሎስም የቀርጤስን ነቢይ ጠቅሶ "የቀርጤስ ሰዎች ዘወትር ውሸተኞች፥ ክፉዎች አራዊት፥ በላተኞች፥ ሥራ ፈቶች ናቸው ብሎአል።"በማለት የራሳቸው ወገን እንኳን የሚመሰክርባቸው አስቸጋሪ ባህርይ ያላቸው ሰዎች እንደሆኑ በቲቶ 1:12 ገልጿል። ከዚህም የተነሳ ቲቶ የተሰጠው ኃላፊነት ከባድ እንድሆነ ግልጽ ነው።

በቀርጤስ አካባቢ ያሉ አቢያተክርስቲያናት ክርስቲያን ነን በሚሉ ነገር ግን በተባላሹና አለምን በሚመመሰልና ስርዓት በጎደለው መልኩ የሚያስተዳድሩ መሪዎች ተፅዕኖ ውስጥ የወደቁ እና የሚተዳደሩ ነበሩ። በዚህ ደብዳቤ ጳውሎስ ቲቶን ይህንን የተበላሸ ስርዓት መልክ እንዲያሲዝ (ቲቶ 1:5) እንዲሁም የማይነቀፉ መሪዎችን እንዲሾም መመሪያ የሰጠበት ነው።

**የመልዕክቱ አላማ፡-**

- ነቀፋ የሌለባቸውና ብቁ የሆኑ ሽማግሌዎችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መለኪያ እንዴት እንደሚሾሙ መምከር(1:5-9)፡፡
- ሕይወት የሚገኝበት/ ትክክለኛ/ ጤናማ ትምህርት (Sound Doctrine) ማሰተማር ቤተክርስቲያን ጤናማ ሆና እንድትቀጥል ማዕከላዊ መሆኑን ማስረገጥ(2:1)፡፡
- ሐሰተኛ አስተማሪዎችን መጋፈጥና መገሰጽ የመንጋውን መንፈሳዊ ጤንነት ለመጠበቅ የቤተክርስቲያን መሪዎች ሊተገብሩ የሚገባቸው ዋና ነገሮች እንደሆኑ ማሳሰብ (1:10-16)፡፡
- አማኞች ለበጎ ሥራ እንዲነቃቁ ለመምከር (2:3-10; 2:14; 3:1; 3:8) እንዲሁም የበጎ ስራ ሁሉ መሰረት ወንጌል እንደሆነ ለማስረገጥ (2:11–14; 3:3–7)፡፡
- ራስን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል ለመኖር ብቁ የሚያደርገው የእግዚአብሔር ጸጋ እንደሆነ ማስታወስ (2:11-12

**ጥናት 1**

## ሰላምታና ሽማግሌዎችን ለመሾም ለቲቶ የተሰጠው መመሪያ

**የምንባብ ክፍል፡- ቲቶ 1:1-9**

**መግቢያ** : በዚህ የመጀመሪያ የቲቶ መልዕክት የጥናት ክፍል ጳውሎስ በቁርጤስ ባሉ አብያተክርስቲያናት ቲቶ ያለተስትካከለ ነገር እንዲያስተካክልና ብቁ ሽማግሌዎችን እንዲሾም የሰጠውን መመሪያ እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ከቁ. 1-4 ባለው ክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ ወይም በአጽንኦት የተጠቀሱ ቃላቶችን በማየት ለደብዳቤው ዋና ሃሳብ ያላቸውን አስተዋጽዎ ተነጋገሩ።
2. ጳውሎስ እራሱንና ቲቶን የገለጸበት አገላለጽ በመዘርዘር ተወያዩ።
3. በ ቁ.1 መሰረት ሐዋርያና ባሪያ የሚሉትን ቃላት መፅሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም በማየት ያላቸውን ተመሳሳይነትናልዩነት ተወያዩ።
4. በቁ.5 ላይ እንደተጠቀሰው ጳውሎስ ቲቶን በቁርጤስ ትቶ የሄደበት ዋና ምክኒያት ምንድነው?
5. ከ ቁ. 6-9 የተጠቀሱትን የቤተክርስቲያን ሽማግሌ/መጋቢ መለኪያዎች በመዘርዘር ሁሉም ሳይነጣጠሉመሟላታቸው ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ተወያዩ ።
6. በቁ. 7 "ኤጲስ ቆጶስ፥ እንደ እግዚአብሔር መጋቢ፥ **የማይነቀፍ** ሊሆን ይገባዋልና" ይላል። የማይነቀፍ የሚለው ሃሳብ ሃጢያት የማይሰራ መሆኑ ግልጽ ነው። ነገርግን በሁለቱ (የማይነቀፍ እና ሃጢያት የማይሰራ)መካከል ያለውንልዩነት ተወያዩ።

- ❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ነገርግን መሰረታዊ የሆነ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜተወያዩ።**

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡-**

7. እራሳችንን እንደ ክርስቶስ ባሪያ ማየት የክርስትና ህይወታችን ላይ የሚያመጥው ተፅዕኖ ምን ሊሆን ይችላል?
8. አጥቢያ ቤተክርስቲያን እግዚብሔርን የሚፈሩና በቲቶ 1:6-9 የተጠቀሱትን ባህርያት የሚያሟሉ መሪዎች ልታፈራየምትችለው እንዴት ነው? እንደ አማኝ የእኛስ ኃላፊነት ምንድነው?

**ማጠቃለያ፡-**

በዛሬው ጥናታችን ቤተክርስቲያንን የሚመሩ ሽማግሌዎች ብቁ የሆኑና ነቀፋ የሌለባቸውን መሆን እንድሚገባቸው ከዚህም ጋር በተያያዘ ለቲቶ የተሰጥውን ከባድ የሆነ ኃላፊነት ተመልክተናል። እኛም እንደ አማኞች ቤተክርስቲያን ብቁ የሆኑ መሪዎችን እድታፈራ ክርስቶስን ወደመምሰል በማደግ ተጽዕኖ ማምጣት ይጠበቅብናል።

**የቃል ጥቅስ**

**፡-**

"ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም፥ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፥ ሽማግሌዎችንእንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ" **ቲቶ** 1:5

**ጥናት 2**

## ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ለቲቶ የተሰጠ መመሪያ

**የምንባብ ክፍል፡- ቲቶ 1:10-16**

**መግቢያ** ባለፈው ጥናት ጳውሎስ በቁርጤስ ባሉ አብያተክርስቲያናት ቲቶ ያልተስተካከለን ነገር እንዲያስተካክልና ሽማግሌዎችን እንዲሾም የሰጠውን መመሪያ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ቲቶለይቶ ማወቅ እንደሚገባውና ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ በተመለከተ ጳውሎስ የሰጠውን ኃላፊነትና ምክር እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ከቁ. 10-16 ጳውሎስ ቲቶ እየመራቸው ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንዲያውቅና እንዲጠነቀቅ ያሳሰበውን አደጋዎች በመዘርዘር ተወያዩ።

    ጳውሎስ በቁ. 15 ላይ "ሁሉ ለንጹሖች ንጹሕ ነው፤ ለርኩሳንና ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም የለም" ሲል ምንማለቱ እንደሆነ ሙሉ ጥቅሱን ከክፍሉ አጠቃላይ ሃሳብ ጋር በማገናዘብ ተወያዩ።

2. ጳውሎስ ከቁ. 10 ላይ የተገረዙትን ከዓመፀኞች፣ ከንቱ ተናጋሪዎችና አታላዮች የለየላቸው ለምንድን ነው?
3. በክፍሉ ውስጥ ከተዘረዘሩት አደጋዎች ውስጥ በአካባቢያችሁ (በዙሪያችሁ) የበለጠ ጎልቶ የምታዩት የትኛውንነው?

- ❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ነገርግን መሰረታዊ የሆነ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜተወያዩ።**

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

4. የሐሰት ትምህርቶችን ለመለየት እና ለመቃወም እንደ አማኝ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

**ማጠቃለያ**

በዛሬው ጥናታችን ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ለይቶ ማወቅና በስህተት ትምህርታቸውም ቤተክርስቲያንን እንዳይበክሉ መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ ተምረናል።

**የቃል ጥቅስ** ፡-

"እግዚአብሔርን እንዲያውቁ በግልጥ ይናገራሉ፥ ዳሩ ግን የሚያስጸይፉና የማይታዘዙ ለበጎ ሥራምሁሉ የማይበቁ ስለ ሆኑ፥ በሥራቸው ይክዱታል።" ቲቶ 1:16

## ጥናት 3

## ለአማኞች የተሰጠ መመሪያ

## የምንባብ ክፍል፦ ቲቶ 2:1-10

**መግቢያ** :ባለፈው ጥናት ጳውሎስ የሐሰተኛ አስተማሪዎች ባህርይ ለቲቶ በዝርዝር ከገለጸ በኋላ ሊወስደው የሚገባውን እርምጃ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ቲቶ ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት የሚገባውን እንዲናገርና አማኞች ደግሞ ሊኖራቸው ሲለሚገባ ባህርይ እንዲያስተምር፣ እንዲመክር፣ እንዲሁም እራሱን አርአያ አድርጎ እንዲያቀርብ ጳውሎስ የመከረውን ምክር እንመለከታለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ጳውሎስ በቁ. 2:1 ላይ ቲቶ እንዲያደርግ እየመከረው ያለው መሰረታዊ ነገር ምንድነው? ሕይወት የሚገኝበት/ ትክክለኛ/ ጤናማ ትምህርት (Sound Doctrine) ማለት ምን ማለት ነው? ቲቶ 2:1
2. ከ ቁ. 2-6 ባለው ክፍል ውስጥ ሽማግሌዎች፣ አሮጊቶች ሴቶች፣ ቆነጃጅት፣ ጎበዞች እና ባሪያዎች ሊኖራቸው የሚገባ ባህርያት ብሎ ዻውሎስ የጠቀሳቸውን በመዘርዘር ተወያዩ።
3. ከላይ የተጠቀሱት ሰዎች የሚገባቸውን ባህርያት እንዲያሳዩ የቲቶ አስተቃጽኦ ምን ሊሆን እንደሚገባ ጳውሎስ ይመክራል?
4. ከ ቁ. 1-6 የተጠቀሱት ሰዎች ባህርያቸው ላይ እንዳይታይ ቲቶ እንድያስጠነቅቃችው ጳውሎስ ያሳሰበውንበመዘርዘር ተወያዩ።
5. ሊያሳዩት የማይገባቸው ባህርያትን በመዘርዘር ቲቶ በአጽንኦት ሊያስጠነቅቃቸው የሚገባበትን ምክንያት ተወያዩ ።

- ❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ነገርግን መሰረታዊ የሆነ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜተወያዩ ።**

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. ጤናማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትን (Sound Doctrine) ለማዳበር በግላችሁ የምታደርጉትን ጥረትለቡድናችሁ አከፍሉ።

**ማጠቃለያ**

በዛሬው ጥናታችን ሕይወት የሚገኝበት ትምህርት ምን ማለት እንደሆነና አማኞች በዚህ ትምህርት ታንጸን የክርስቲያንባህርይን በምላበስ የማያምን ሳይቀር የሚነቅፍብን ነገር እንዲያጣ መመላለሰ በጥንቃቄ መመላለስ ይኖርብናል ።

**የቃል ጥቅስ**

"አንተ ግን ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት የሚገባውን ተናገር።" ቲቶ 2:1

## ጥናት 4

## ቅዱስ ጥሪ እና የአማኞች ሃላፊነት

## የምንባብ ክፍል፦ ቲቶ 2:11-15

**መግቢያ** :ጳውሎስ ህይወት የሚገኝበትን ትምህርት ለሽማግሌዎች፣ ለአሮጊቶች፣ ለወጣት ሴቶች፣ እና ለወጣት ወንዶች በዝርዝር እንደነገራቸው አጥንተናል። ዛሬ ደግሞ ለደህንነት የሆነውን ቅዱስ ጥሪ፣ የእምነታችንን ተስፋ፣ እንዲሁም የቤተክርስቲያንን ሃላፊነትን እንማራለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በአለም ላይ ምን ተገለጠ (2፡11)? በሰዎች ላይ ምን ተጽእኖ አሳድሯል?
    - 'የእግዚአብሄር ጽጋ" ማለት ምን ማለት ነው ወይስ ምንን ያመለክታል? (2:11)?
    - 'ሰዎችን ሁሉ የሚያድን' ሲል ሰው ሁሉ ይድናል ማለት ነው (2፡11)? እንዴት አወቅክ?
2. ከቁ12-14 የእግዚአብሄር ጸጋ ሲለውጣቸው በእውነተኛ አማኞች ላይ የሚደርሰውን ለውጥ ዘርዝር።
    - 'ዓለማዊን ምኞት' ምንድነው? ምሳሌ አቅርብ።
3. እግዚአብሔር ጽጋውን ወደ ዓለም ያመጣባቸው ዓላማዎችን ዘርዝር (2፡14) ።
    - ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሶስት ሃረጎች አብራራ
        --"ራሱን ለእኛ ሰጠ' የሚለውን ሃረግ ምን ማለት ነው?
        --'ከአመጽ ሁሉ እንዲቤዠን
        --'መልካሙን ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ህዝብ'
4. 'ይህንን በሙሉ ስልጣን ተናገር' ይላል። "ይህንን" የሚለውን ሃሳብ በዝርዝርአብራራ (2፡15) ።
    - 'በሙሉ ስልጣን' መናገር ምን ማለት ነው?

❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ነገርግን መሰረታዊ የሆነ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜተወያዩ።**

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

5. የተባረከውን ተስፋችንን (የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት) የምትጠባበቁት በምን አይነት ሁኔታ ነው?
6. ለበጎ ስራ ለመነቃቃት እንዲረዳችሁ በእለት ተለት የክርስትና ጉዟችሁ የምታደሩትን ጥሩ ልምድ ለቡድናችሁአካፍሉ።

**ማጠቃለያ**

በዛሬው ትምህርታችን ቤተክርስቲያን (የእግዚአብሄር እውነት ያለው ህዝብ) አንዳንድ ጊዜ የማይለወጡት ለምንድነው የሚለውን ያስተምረናል። እርሱም ከሃጢያተኛነት የምንድንበትን ጸጋ እና ከዓመጻ ሁሉ እንድንድን ራሱን እንደሰጠን ተምረናል።

**የቃል ጥቅስ**

"ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሄር ጸጋ ተገልጦአል፣" ቲቶ 2፡11

## ጥናት 5

## ክርስቶስን መምሰል

## የምንባብ ክፍል፦ ቲቶ 3፡1-8

**መግቢያ**: ባለፈው ሳምንት ዓለማዊ ምኞትን አንድናሸንፍ ጌታችን እንዳዳነንና ጸጋንም እንደሰጠን ተመልክተናል። ዛሬ ደግሞ አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን አማኙ በጎ የሆነውን በማድረግ ክርስቶስን የሚመስል ህይወት ሊኖር እንደሚገባ እንማራለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ጳውሎስ ቲቶን በቁጥር 3፡1-2 ላይ “”…አሳስባቸው ብሎ የተናገረው እነማንን ነው? የሚያሳስባቸውንስ ምንንነው?
   - ‘…የማይከራከሩ…’ ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ጳውሎስ ‘እኛ ደግሞ አስቀድመን …’ በማለት ህይወታችንን የገለጸው እንዴት ነው (3፡3)?
   - ‘እኛ …’ ማንን ያመለክታል? ለምን? ሁሉም አማኞች ከክፋት፣ ከምቀኝነት፣ ከምኞት ባርነት ነጻ ነን ማለት ነው?
3. በህይወታችን ውስጥ እንዲህ ያለ ለውጥ ማምጣት የቻለው የትኛው ታሪካዊ ክስተት ነው (3፡4-5)?
4. ጳውሎስ አንድ ሰው የሚድንበትን መንገድ የገለጸው እንዴት ነው (3፡5)?
   - ‘ኢየሱስ አዳነኝ’ የሚለውን ሃረግ ብዙ ጊዜ እንሰማለን። ቲቶ 3፡4-5 ላይ ያለው ክፍል በእርግጥ ይህንንእንድንጠቀም ያበረታታልን? እንዴት?
   - ‘የአዲስ ልደት መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ፣ በጸጋ መጽደቅ’ የሚሉትን ሃረጎች በአዲስ አማኝ ላይየሚደረጉትን መንፈሳዊ ለውጦች የሚገለጸው እንዴት ነው (3፡5-6)?
5. መጽደቅ ምን ውጤት አለው (3፡7)? በዝርዝር ግለጽ።
   - ‘በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ህይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን’ (3፡7) የሚለው ሃረግ ምን ማለቱ ነው? ወይንምጳውሎስ <u>የአማኞችን ርስት</u> ለመግለጽ <u>ከዘላለም ህይወት</u> ጋር ማዛመዱ ምንን ለማመልከት ነው።
6. ጳውሎስ ቲቶ 3:8 ላይ ምን እንዲያደርግ ነግሮታል?
   - “ይህ ቃል የታመነ ነው” (3:8) ብሎ መናገሩ ያስፈለገው ለምን ይመስልሃል?
7. ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች ለቲቶ የነገረበት  ዓላማ ምን ይመስልሃል?

❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ነገርግን መሰረታዊ የሆነ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜተወያዩ።**

**<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>**

**<u>ማጠቃለያ</u>**

በክርስቶስ በኩል ያለው መዳን እና በአማኝ ሕይወት ውስጥ ያለው አስደናቂ ተፅእኖ በመዳን ጊዜ ብቻ ሳይሆን በምድር ላይህይወቱና እና እስከ ዘላለማዊነት ርስቱ እስኪሄድ ድረስ ያለውን ተጽእኖ ተምረናል።

**<u>የቃል ጥቅስ</u>**

“እንደ ምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፤እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤” ቲቶ 3: 5

## **ጥናት 6**

## **የመጨረሻ ሰላምታ እና ምክር**

## **የምንባብ ክፍል፦ ቲቶ**

**3፡9-15**

**መግቢያ:** ባለፈው ሳምንት የእግዚአብሄር ምህረትና ቸርነት በመንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደጸደቅን በዝርዝር ተምረናል። ዛሬ ደግሞ ከዳንን በኋላ ልንርቀው የሚገባንንና ደግሞ ቤተክርስቲያን ሃላፊነቷ በመሆኑ አጥብቃ ልጸራው የሚገባ ነገር ምን እንደሆነ እንማራለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቁ.9 ጳውሎስ የዘረዘራቸውን 4 ችግሮች ጥቀስ/ሺ (ዘርዝር/ሪ)።
   - እነዚህ ችግሮች እያንዳንዳቸው ከሌላው እንዴት እንደሚለያዩ ግለጽ/ጪ (3፡9)።
   - እነኚህ የመንስኤ እና ውጤት (Cause and Effect) ግንኙነት አላቸው? አብራራ/ሪ።
   - ጳውሎስ እነኚህን ለምን ለቲቶ የማይጠቅሙ መሆናቸውን የነገረው ይመስልሃል/ሻል (3፡9)?
2. ጳውሎስ "መለያየትን የሚያነሳ ሰው" በቤተክርስቲያን ውስጥ ምን እንዲደረግ ያስተምረናል **(3፡10)?**
   - "እንዲህ ከሚመስል ሰው ራቅ" ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - "በራሱም ላይ ፈርዶ..." ሲል ጳውሎስ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
3. ከቁ 12-15 ላይ ጳውሎስ የተናገራቸውን የተለያየ ርዕሰ ጉዳዮች ዘርዝር/ሪ።
   - ይህ ከቲቶ ጋር ስላለው የግል/የስራ ግንኙነት ምን ያሳየናል?
   - ጳውሎስ ክርስቲያኖች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለቲቶ ነግሮታል? (3:14)
   - ቁጥር 13 እና 14 ላይ ያለውን አጠቃላይ መመሪያ የሚያሳየው እንዴት ነው?

❖ **በዛሬው የንባብ ክፍል ውስጥ በመወያያ ጥያቄዎቹ ያልተዳሰሰ ነገርግን መሰረታዊ የሆነ ሀሳብ ካለ በቀራችሁ ጊዜ ተወያዩ።**

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

4. መለያየትን የሚሰብክ ሰው አጋጥሟችሁ ከሆነ በምን መልኩ እንደመከራችሁ እንደገሰጻችሁ ወይም ምን አይነት እርምጃ እንደወሰዳችሁ ለቡድናችሁ አካፍሉ።

**ማጠቃለያ**

በዛሬው ጥናታችን ሞኝነት ካለው ምርመራ፣ መለያየትን ከሚያሰፍን ሰው እንድንርቅና ይልቁንም ወገኖች የሆኑትን ፍሬያማህይወት እንዲኖራቸው በዚህም ቤተክርስቲያን ለእግዚአብሄር ክብር የሚሆን ፍሬን ልታፈራ እንደሚገባ ተምረናል።

**የቃል ጥቅስ**

" ከወገናችንም ያሉት ደግሞ ፍሬ ቢሶች ሆነው እንዳይቀሩ፥ የግድ ስለሚያስፈልገው ነገር በመልካም ሥራ እንዲጸኑ ይማሩ ። " ቲቶ 3:14